# ለሌሎች ማስተላለፍ!

# ክርስቶስን ማዕከል ላደረገ መሪነት የሚደረግ እንቅስቃሴ መሰረት

መጽሐፍ ቅዱሳዊ በሆነ እሴት፣ ስልት እና ልምምድ ለግል ሕይወት መለወጥ፣ ለተቋማዊ ለውጥ እንዲሁም ለአገልግሎት መስፋት መሪዎችን ማስታጠቅ፡

MentorLink International

www.mentorlink.org

# ማውጫ

ክፍል 1 - ክርስቶስን ማዕከል ያደረጉ መሪዎችን የማሳደግ አስፈላጊነት ........ 1
የቤተክርቲያን ወሳኝ የሆነ ፍላጎት........ 1
በአርአያነት መምራት ምንድነው?........ 2
ለውጥ በሚያመጣ አርአያነት የመምራት ትርጉም........ 2
ክፍል 2 - ክርስቶስን ማዕከል ያደረጉ መሪዎች በማሳደግ ሂደት ውስጥ ያሉ ዋና ዋና ነገሮች ........ 3
ፍጹም የአመለካከት ለውጦች........ 4
የእሴት ለውጥ #1:የእግዚአብሔርን መንግስት መገንባት ........ 4
በቤተሰብ ውስጥ በዓርአያነት መምራት........ 7
የእሴት ለውጥ #2፡የፀጋ አገልግሎት ........ 10
የእሴት ለውጥ #3፡አገልጋይ መሪነት........ 13
የእሴት ለውጥ #4: ትብብር እና ማህበረሰብ........ 16
የእሴት ለውጥ #5: መሪዎችን አስቦ ማብዛት ........ 19
ክፍል 3 – ክርስቶስን ማዕከል ያደረጉ መሪዎችን በማሳደግ ውስጥ የሚያስፈልጉ ችሎታዎች ........ 22
ታሪካችሁን መናገር........ 22
በአርአያነት የመምራት ግንኙነት የመመስረቻ ደረጃዎች ........ 23
ክፍል 4 -ክርስቶስን ማዕከል ያደረጉ መሪዎችን በማሳደግ እንቅስቃሴ ውስጥ ከእግዚአብሔር ጋር መተባበር ........ 24
በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉት የእግዚአብሔር እንቅስቃሴዎችና በአሁኑ ጊዜ ያሉት እንቅስቃሴዎች ........ 24
ከድርጅት ባህል ጋር የሚገናኙ ጉዳዮች እና ፈተናዎች ........ 26
የተግባር ዕቅድ........ 29
ለአሰልጣኞች ቡድን ያላችሁ ጥቆማ........ 32

MentorLink International በክርስቶስ በኩል እናንተን ማገልገሉን እንደ መልካም ዕድል ይቆጥራል። ይህ የመመሪያ መፅሀፍ በብዙ ሰዎች አማካኝነት የተዘጋጀ ሲሆን በአለም ዙሪያ በሚገኙ የተለያዩ ሀገራት የተተገበረ ነው።

እኛ እናንተን ለማገልገል በተነሳ ልብ ነው የመጣነው። በአርአያነት ለመምራትና የክርስቶስ አይነት መሪነት ለማሳደግ በመሰጠታችሁ ምክንያት እግዚአብሔርን በምታገለግሉበት ቦታ ይህ ነገር እንዲበቅል ፀሎታችን ነው።

The MentorLink Leadership Team

ይህንን መመሪያ ይዘቱ ሳይቀየር ኮፒ አድርጎ መጠቀም የተፈቀደ ነው። በድጋሚ የተከለሰው ህዳር 8፣ 2003 ዓ.ም



© 2016 MentorLink International

# ክፍል 1 - ክርስቶስን ማዕከል ያደረጉ መሪዎችን የማሳደግ አስፈላጊነት

## የቤተክርቲያን ወሳኝ የሆነ ፍላጎት

ተልዕኳችን፡ ኢየሱስን ማዕከል ያደረጉና ኢየሱስን የሚመስሉ መሪዎችን በአማኙ ማህበረሰብ መካከል ማስነሳት

ራዕያችን፡ ለእያንዳንዱ አማኝ ማህበረሰብ ክርስቶስን ማዕከል ያደረገና ክርስቶስን የሚመስል መሪ ማብዛት




- እንደኢየሱስ መምራት - ከ «ውስጥ ወደ ውጪ» እና ከታች ወደላይ አመራርን ማሳደግ
  - በግል ባህሪያችን ላይ እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ለመሆን ትኩረት ማድረግ
  - በአገልግሎት ስልታችን እንደ ኢየሱስ ለመሆን መትጋት

- ውጤቱ - ለእግዚአብሔር መንግስት ስራ የእንግዚአብሔር መንግስት መሪዎች ማደግ
  - ብልጫ ያለው የመሪዎች ጥራት
  - ብልጫ ያለው የመሪዎች ብዛት


© 2016 MentorLink International

ወደዚህ «የፍጹም ለውጥ» ጎዳና ይሆናል ብለን ተስፋ ወደምናደርገው ልምምድ እንኳን ደህና መጣችሁ፡፡ በእነዚህ ቀናቶች በሚኖረን የህብረት እድገት እግዚአብሔር በመሀከላችን እንዲገኝ እንጠይቀዋለን፡፡ በዚህም ሒደት በሚኖራችሁ የማሰብ፣ የማጥናት፣ የመነጋገር፣ በህብረት የመፀለይ እድል በአርአያነት የሚመራው ቡድን እጅግ አስፈላጊ የሆነ ሚና ይጫወታል፡፡

## በአርአያነት መምራት ምንድነው?

### ሁለት ጥያቄዎች

1. በህይወታችሁ አብላጫውን መንፈሳዊ ተፅዕኖ ያመጣውን ሰው ጻፉ

2. ተፅዕኖ የፈጠረባችሁ የእነዚህ ሰዎች ምናቸው ነው ?

### መጽሐፍ ቅዱሳዊ አርአያነት

ከዚህ በታች ያሉትን ጥቅሶች ለማንበብና በእነርሱ ዙሪያ ለመወያየት ጊዜ እንውሰድ፡፡

- ዩሐ 13፡5-15
- ዮሐ 15፡13-16
- የሐ.ሥራ 11፡21-26
- የሐ.ሥራ 18፡24-27
- 2ጢሞ 3፡10-15
- 2ጢሞ 2፡1-12

ከእነዚህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክፍሎች ከዚህ በታች ባሉት ጥያቄዎች አማካኝነት ስለ አርአያነት ያላችሁን ሀሳብ በማስታወሻችሁ ላይ መዝግቡ፡

1. ውጤታማ በአርአያነት የሚመራ ሰው ባህሪዎች ምን ምን ናቸው?

2. በአርአያነት በመምራት ሂደት ውስጥ በአርአያነት የሚመራው ሰው ተግባራት ምንድን ናቸው።

3. በአርአያነት የመምራት ሂደት ውጤቱ ምንድነው?

## ለውጥ በሚያመጣ አርአያነት የመምራት ትርጉም

***ለውጥ በሚያመጣ አርአያነት መምራት*** ማለት፡- የአንድ ሰው የሕይወት ጉዞ አካል ለመሆንና ከእግዚአብሔር መሳሪያዎች ውስጥ አንዱ በመሆን ያንን ሰው እግዚአብሔር የሚፈልገውን አይነት ሰውና


© 2016 MentorLink International

እግዚአብሔር እንዲሰራ የሚፈልገውን የሚሰራ ሰው ወደ መሆን እንዲመጣ ለመርዳት ተነሳሽነት መውሰድ ማለት ነው፡፡

1. **<u>ተነሳሽነት</u> መውሰድ**፡- የሚከተለውን ለማድረግ ሆን ብዬ እመርጣለሁ
   - ☐ በአርአያነት የመምራት አገልግሎቴ ላይ እግዚአብሔር ልቡንና ምሪቱን እንዲሰጠኝ መጸለይ
   - ☐ እግዚአብሔር ለኔ የሰጠኝን ለሌሎች የማስተላለፍ አመለካከት ባለቤት መሆን
   - ☐ ቅድሚያ የምሰጣቸውን ነገሮች በማስተካከል «በአርአያነት ለመምራት» ጊዜ ማመቻቸት
   - ☐ በአርአያነት ለመምራት ሲባል ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮችና ጊዜ ማመቻቸት
   - ☐ አርአያ የሚሆኑና አርአያ የሚያስፈልጋቸውን ሰዎች መለየት

2. **የአንድ ሰው የሕይወት ጉዞ <u>መቀላቀል</u>**
   - ☐ ተከታታይ በሆነ መንገድ የአንድነት ጊዜን በጋራ ማሳለፍና እምነታቸውን ማግኘት
   - ☐ ወደ ጠለቀ ግንኙነትን ሌሎችን ለመጋበዝ የእኔን የግል ሕይወትና ታሪክ በተገቢዉ መንገድ ማካፈል
   - ☐ የሌሎችን ሀሳብ በደንብ ለመረዳት ጥያቄዎችን መጠየቅና የልባቸውን ለመረዳት ማዳመጥ፡፡
   - ☐ እድገት የሚያስፈልጋቸው አቅጣጫዎችን ለመመልከት የተከታዮችን ዋና ዋና የግንኙነት መስመሮች መገምገም (እግዚአብሔር፣ ቤተሰብ፣ ጊዜ፣ ገንዘብ፣ አገልግሎት ወዘተ...)

3. **ሌሎችን ለመርዳት ከእግዚአብሔር መሳሪያዎች ውስጥ አንዱ <u>መሆን</u>**፡- በምሳሌነት መምራት ሂደት..
   - ☐ እንደክርስቶስ ተከታይ የዕድሜ ልክ በሆነ የማያቋርጥ ትምህርትና እድገት ምሳሌ መሆን፡፡
   - ☐ በአርአያነት ለምመራቸው ሰዎች ስለ ግል እድገቴ፣ የህይወት ትግልና የኑሮ ጉዳዮች ግልጽና ሀቀኛ መሆን
   - ☐ በተማሪዎች ወይም ተመሪዎች ህይወት ውስጥ ተጽእኖ ካላቸው ሌሎች ሰዎች ጋር በመተባበር መስራት
   - ☐ በግንኙነቶቻችን ከተቆጣጣሪነት አመለካከት ይልቅ የአገልጋይነት ልብ ባለቤት መሆን

4. **እግዚአብሔር የሚፈልገው አይነት ሰውና እንዲሰራ የሚፈልገውን የሚሰራ ሰው ወደ መሆን እንዲመጣ መርዳት**
   - ☐ እግዚአብሔር በህይወታቸው እራሱንና ጥሪውን እንዲገልጽ መጸለይ
   - ☐ እግዚአብሔር የሰጣቸውን ስጦታና ጥሪያቸውን እንዲለዩና እንዲያሳድጉ መርዳት፡፡ (ስጦታ፣ችሎታ፣ ዝንባሌ
   - ☐ እኔ ላበረከተው ከምችለው አስተዋጽኦ በላይ እንዲያድጉ መልቀቅ
   - ☐ ብቻውን ለውጥ ማምጣት ከሚችለው አባትጋር በመተባበር ለሌሎች አርአያ እንዲሆኑና ሌሎችን እነዲያፈሩ መገፋፋት

## ክፍል 2 - ክርስቶስን ማዕከል ያደረጉ መሪዎች በማሳደግ ሂደት ውስጥ ያሉ ዋና ዋና ነገሮች

**መንፈሳዊ «ጉድለቶቻችን»**

ሁላችንም መጽሐፍ ቅዱስ «ሥጋ» ብሎ የሚጠራው ተፈጥሮአዊ የሆነ መንፈሳዉ ጉድለቶች አለን፡፡ ሥጋ አካላዊ ማንነታችንን ይወክላል ይህም የድሮ ትውስታችንንና የወደቀው ሰው ልምምዶችን ያካትታል፡፡

**ስጋ ከመንፈስ ጋር ሲነፃጸር**

አንድ ሰው ዳግም ሲወለድ አዲስ ነገር እውን ይሆናል፡፡ በመንፈስ ቅዱስ መገኘት አዲስ ባህሪና ብቃት አለን፡፡ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ላይ ካልተደገፍን «የድሮው ማንነታችን» እራሱን ይገልጣል፡፡ (ገላ 5፡16-25፤ ሮሜ 8፡1-13)

**ስጋዊ መሪነት**

በማንኛውም ባህል፣ ቋንቋ ወይም ቤተ-እምነት ቢሆን ክርስቲያን መሪዎች ከአለማዊ መሪዎች ጋር ተመሳሳይ ስጋዊ መገለጫዎችን ሲጋሩ ይታያሉ፡፡ ቁጥጥር፣ ስልጣን፣ ግብዝነት፣ ክብርና ሌሎችም፡፡ እንደ ኢየሱስ የሚመራ መሪ በመንፈስ ቅዱስ ሀይል እየተራመደና የበፊት አመለካከቶቹን በመተው ክርስቶስን ይከተላል፡፡


© 2016 MentorLink International

## ፍጹም የአመለካከት ለውጦች

| ስጋዊ የመሪነት አመለካከቶችንና ልምምዶችን ከኋላ መተው | | መንፈሳዊ የመሪነት አመለካከቶችንና ልምምዶችን ይዞ ወደፊት መጓዝ |
|---|---|---|
| **የግል ውጤታማነትን መገንባት**<br><br>እግዚአብሔር በዋነኛነት በእኔ በአገልግሎቴ ወይም በድርጅቴ ስራውን እየሰራ እንደሆነ ማሰብ፤ በግል መንቀሳቀስ፤ የሌሎች አስፈላጊነት አነስተኛ እንደሆነ ማሰብ | → | **የእግዚአብሔርን መንግስት መገንባት**<br><br>ስለ እግዚአብሔር መንግስት ሁለንተናዊ መረዳት፤ የክርስቶስን ክብር የሚፈልግና የመንግስቱን ሥራ የሚያስተዋውቅ አመለካከት ባለቤት መሆን |
| **በቁጥጥር የተሞላ ሁኔታ**<br><br>ፉክክርን የተቃውሞ አመለካከትን እኔ እበልጣለሁ ባይነትን ክብርን እና/ወይም ውድቀትን ሊፈጥር በሚችል፤ ስራ ላይ ወይንም ቁጥጥር ላይ በሚያተኩር መንገድ መኖርና መምራት:: | → | **በጸጋ የተሞላ ሁኔታ**<br><br>ክርስቶስ በጨረሰው ስራ ላይ የተመረኮዘ መሪነት፤ ራስን ዝቅ በማድረግ፣ በግልጽነትና በፍቅር መምራት:: በመቀበል በይቅር ባይነት በእውነተኛነትና በተጠያቂነት ሌሎችን መምራት |
| **ስልጣንን መሰረት ያደረገ መሪነት**<br><br>በቦታ፣ ስልጣን፣ እንዲሁም ፓለቲካዊ ተጽእኖ መምራት:: አብዛኛውን ጊዜ ቁጥጥርና ድርጅታዊ ስልጣን ማዘውተር:: ሌሎችን የማመንና ለማስታጠቅ ያለመፈለግ ችግር መታየት::. | → | **የአገልጋይነት መሪነት**<br><br>መተማመን ባለበት ግንኙነቶች በእኩልነት እንዲሁም በአገልግሎት ሌሎችን መምራትና ተጽእኖን ማሳደር:: የሌሎችን ፍላጎት ለሟሟላትና ውጤታማ እንዲሆኑ ለማድረግ እራስን መስጠት |
| **እኔ እበቃለሁ ባይነት**<br><br>በሁሉም የመሪነት ሀላፊነት ሁኔታ ውስጥ ብቁ ሆኖ ለመገኘት መሞከር:: ጫና ያለበትና በግንኙነት ራቅ ያለ አኗኗር ለመኖር መሞከር።ከሌሎች ጋር በጋራ የመስራት ችግር::. | → | **በትብብርና በጋራ መስራት**<br><br>የእግዚአብሔርን ስራ ለመስራት የሚተባበር ቡድን አካል በመሆን መምራት:: ህብረትን በመፍጠር ሌሎችን ማሳመን የጋራ ተጠያቂነት እና ውክልና በመስጠት ሌሎችን በማስታጠቅ መምራት:: |
| **በድንገተኛ ሁኔታ ሌሎች መሪዎችን መጨመር**<br><br>ጥቂትና በቂ ያልሆኑ መሪዎች በተለመደው ቀጥተኛ መንገድ ላይ በመመርኮዝ ያድጋሉ:: ይህ መንገድ ስሩን የሰደደው ማብዛት ላይ በማተኮር ነው:: | → | **የታቀደበት መሪዎች ማብዛት**<br><br>ተሰጥያው ያላቸውንና የልባቸው ፍላጎት የእግዚአብሔርን መንግስት ማስፋት የሆኑ መሪዎችን በማብዛት አመራርን ማሳደግ። |

ኢየሱስ እንዲህ አለ መልካምነት ክብደት ስላለው በፍጥነት ትንሽን ስልጣን በመጠቀም በሰው አዕምሮ ያለውን ተጽእኖ ተመርኩዞ ሲመራ ተመለከታችሁ:: ነገር ግን በእናንተ ዘንድ እንደዛ አይደለም:: ማቴ 20፡25-26

### የእሴት ለውጥ #1:የእግዚአብሔርን መንግስት መገንባት

***የግል ውጤትን ከመገንባት የእግዚአብሔርን መንግስት ወደ መገንባት***

«. . . ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔር መንግስት ጽድቁንም ፈልጉ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል» ማቴ 6፡33

በክርስቶስ ኢየሱስ ፍጹም የተቀየረ መሪ . . . አትኩሮቱ የግል ውጤታማነት ከመገንባት እራሰን አገልግሎቱን ወይም ድርጅቱን ከማስተዋወቅ የእግዚአብሔርን መንግስት ወደ መገንባት የክርስቶስን ክብር ወደ መጠማትና እያንዳንዱን የህይወት የአገልግሎትና የባህል አቅጣጫ በሚነካ መልኩ የእግዚአብሔርን መንግስት ማስተዋወቅን ወደ መፈለግ እየተቀየረ ያለ ሰው ነው::


© 2016 MentorLink International

## መንግስት መገንባት

*አንድ የታሪክ ጥናት ከብዙይ ኪዳን*

**ዲዮጥራጢስ**

የእግዚአብሔርን ሳይሆን የራሱን መንግስት የሚገነባ መሪ

ወደ ቤተክርስቲያን ፃፍሁ ዳሩ ግን ዋናቸው ሊሆን የሚወድ ዲዮጥራጢስ አይቀበለንም፡፡ ስለዚህ እኔ ብመጣ በእኛ ላይ በክፉ ቃል እየለፈለፈ የሚያደርገውን ስራውን አሳስባለሁ፡፡ ይህም ሳይበቃው እርሱ ራሱ ወንድሞችን አይቀበልም ሊቀበሏቸውም የሚወዱትን ከልክሎ ከቤተክርስቲያን ያወጣቸዋል፡፡

ወዳጅ ሆይ በጎ የሆነውን እንጂ ክፉውን አትምሰል፡፡ 3 ዮሐ 9-11

ለምን ነበር ዲዮጥራጢስ ተቃውሞ የደረሰበት? (9-10)

ስለ ክፉ ምኞቶች የዮሐንስ ማስጠንቀቂያ ምንድነው? (11)

## «የእግዚአብሔር መንግስት ግንባታ»

*አንድ የታሪክ ጥናት ከብሉይ ኪዳን*

**ጢሞቲዎስ**

የእግዚአብሔርን መንግስት እንጂ የራሱን ያልገነባ መሪ

«ነገር ግን ኑሮአችሁን ሳውቅ እኔ ደግሞ ደስ እንዲለኝ ፈጥኜ ጢሞቲዎስን ልልክላችሁ በጌታ በኢየሱስ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ እንደ እርሱ ያለ ስለ ኑሮአችሁ በቅንነት የሚጨነቅ ማንም የለኝምና ሁሉ የራሳቸውን ይፈልጋሉና የክርስቶስ ኢየሱስን አይደለም ነገር ግን ልጅ ለአባቱ እንደሚያገለግል ከእኔ ጋር ሆኖ ለወንጌል እንዳገለገለ መፈተኑን ታውቃላችሁ፡፡»

ፊልጵስዮስ 2፡19-21

- ጢሞቲዎስ የታዘዘው ትዕዛዝ ምን ነበር? (19-21)
- ስለዚህ ሰማያዊ ፍላጎት የጳውሎስ ደስታ ምንድነው? (ቁ 22)

## የእግዚአብሔርን መንግስት መሪዎችን በአርአያት የመምራት ሂደት

ጴጥሮስ የእግዚአብሔርን መንግስት ለመመስረት በኢየሱስ ተመርጦ የተለየ ሃላፊነት ተሰጥቶት ነበር፡፡ ነገር ግን ይሄ ማለት ጴጥሮስ የግል ፍላጎቱን እንዳይከተል ማበረታቻ ተጠያቂነት እንዲሁም እርማት ከአምላኩ፣ ከአዳኙ፣ ከመምህሩ ክርስቶስ ኢየሱስ ከዚህ በኋላ አያስፈልገውም ነበር ማለት አይደለም፡፡

በማቴ 16፡13-28 የፍጹም ለውጥ በአርአያነት መምራት ሂደትን ተመልከቱ

- የጴጥሮስ ኑዛዜ አስፈላጊነት ለምን ነበር? (15-17)
- ጴጥሮስ ወደ ስጋዊ አመለካከቱ እንዴት ተመለሰ? ኢየሱስ ለዚህ ምን ምላሽ ሰጠ? (22-23)


© 2016 MentorLink International

- ይህ ከባድ ተቃውሞ የጴጥሮስን ብቃት ወይንም በእግዚአብሔር መንግስት የነበረውን የመሪነት ቦታ ገድቦታል? የኢየሱስ ቃላት ለጴጥሮስና ለሌሎቹ ማበረታቻ የሆኑት እንዴት ነበር? (24-28)

ጴጥሮስ የእግዚአብሔር መንግስት መሪነት አእምሮ በመያዝ እያደገ ሳለ ለቤተክርስትያን በእግዚአብሔር መንግስት ግንባታ ላይ የሰጠውን ማስጠንቀቂያ አስተውል የሀሰት አስተማሪዎችና መሪዎችን በ 2ጴጥሮስ 2፡1-3 ውስጥ አስተውሉ

- ጴጥሮስ ቤተክርስቲያንን ስለ ሀሰት መምህራን ሲያስጠነቅቅ ጠንካራ የመሆን ነፃነት ለምን ተሰማው? (1-2)

- በክርስቶስ ቤተክርስቲያን ውስጥ መሪዎች እንደመሆናችን መጠን ራሳችን ከምንድነው መጠበቅ ያለብን? ማበረታቻስ ከምን እናገኛለን?

## *በእግዚአብሔር መንግስት ወይም በግላዊ ውጤት ግንባታ አመለካከት ለውጥ ላይ የቅርብ እይታ ማድረግ*

**በየቡድናችሁ በዚህ የአመለካከት ለውጥ ዙሪያ ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች ተወያዩባቸው፡**

1. ይህ የአመለካከት ለውጥ በአጠቃላይ ስለምንድነው? በራሳችሁ ቃል ግለጹ፡፡

2. ይህንን የአመለካከት ለውጥ በተመለከተ በሀገራችሁ ስላለው የመሪነት ባህል የግል አስተያየታችሁ ምንድነው

### የፍጹም ለውጥ እሴት #1 የግል ግምገማ

ከዚህ በታች ባለው የፍጹም ለውጥ እሴት ባስተሳሰባችሁ ባመለካከታችሁ እንዲሁም በልምምዶቻችሁ የቱ ጋር እንዳላችሁ ገምግሙ፡፡ በመሀከለኛው ክፍል ላይ ካሉት ቁጥሮች ለእናንተ በተሰጡት ጥንድ ሀሳቦች አኳያ የቱ ጋር እንዳላችሁ በመክበብ አሳዩ፡፡ ለምሳሌ በስተግራ ባለው ሰንጠረዥ ውስጥ ያለው ሀሳብ የአብዛኛውን ጊዜ ማንነታችሁን የሚገልጽ ከሆነ ለራሳችሁ «1» ስጡ በቀኝ ያለው ከሆነ ደግሞ «10» ስጡ በመሀከል ካላችሁ «5» ስጡ በተጨማሪም ከበታች ላሉት እራስን የመገምገሚያ ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡

| የግል ውጤትን መገንባት | ... ወደ ... | የእግዚአብሔርን መንግስት መገንባት |
|---|---|---|
| ስለ እግዚአብሔር መንግስትና እሴቶቹ ግልጽ የሆነ መረዳት የለኝም | የእግዚአብሔርን መንግስት መረዳት<br>*1-2-3-4-**5**-6-7-8-9-10* | የእግዚአብሔርን መንግስት ተረድቼዋለሁ ምንም አይነት ዋጋ ቢያስከፍለኝ መስዋዕትነት በመክፈል ልገነባውም እፈልጋለሁ |
| አገልግሎትን የእኔን ስራ የእኔን ቤተክርስቲያን የእኔን ቤተሰብ እንደ እግዚአብሔር መንግስት እግዚአብሔር ለእኔ የሰጠው እንደሆነ ማሳየትን አዘወትራለሁ | ባለቤትነት<br>*1-2-3-4-**5**-6-7-8-9-10* | አገልግሎቴ፣ ስራዬን፣ ቤተክርስቲያኔ፣ ቤተሰቤ ... ወዘተ የእግዚአብሔር ናቸው፡፡ እርሱ ሰጠኝ መልሶ ሊወስድም ይችላል፡፡ የሆነው ቢሆን ስሙን እባርካለሁ |
| መታየትን እፈልጋለሁ፡፡ ሰለዚህ አገልግሎቴ የሚያተኩረው ጥሩ ሆኖ መታየትና የራሴን ስም መገንባት ላይ ነው | ***ክብር***<br>*1-2-3-4-**5**-6-7-8-9-10* | አገልግሎቱ ሙሉ በሙሉ ስለ እግዚአብሔር ነው፡፡ ትልቁ የውስጥ ፍላጎቴ እርሱ እንዲከብርና እንዲመሰገን ነው |


© 2016 MentorLink International

| | | |
|---|---|---|
| ለጥሩ ውጤት መመስገን አለብኝ፡፡ ለውድቀት ደግሞ ሌሎች ሊጠየቁ ይገባል | ***ውጤታማነትና ውድቀት***<br>*1-2-3-4-**5**-6-7-8-9-10* | ምስጋናን እግዚአብሔር ይወስዳል እኔ ደግሞ ለሰራሁት ስህተትና ውድቀት ተጠያቂ እሆናለሁ |
| አብዛኛውን ጊዜዬንና ሀይሌን የማውለው የራሴን መንግስት ለመገንባት ነው | ቅድሚያ የሚሰጣቸው ነገሮች<br>*1-2-3-4-**5**-6-7-8-9-10* | አብዛኛውን ጊዜዬንና ሀይሌን የማውለው የክርስቶስን መንግስት መገንባት ላይ ነው |
| በአጋርነት ለመስራት ፍላጎቱ ጊዜው ወይም አቅርቦቶቹ የሉኝም። አገልግሎቱን ከሌሎች አገልጋዮችና አገልግሎቶች ጋር የመወዳደሪያ ሜዳ አድርጌ ነው የማየው | ***አጋርነት***<br>*1-2-3-4-**5**-6-7-8-9-10* | በትብብር እሰራለሁ ምንክያቱም እግዚአብሔር አካላቶቹ በህብረት በትብብር ሲሰሩ ይባርካልና |
| ፀሎት ጥሩ ነገር ነው ነገር ግን እጅግ በጣም በስራ የተጠመድኩ ስለሆንኩ ቅድሚያ የምሰጠው ነገር አይደለም | የፀሎት ቀዳሚነት<br>*1-2-3-4-**5**-6-7-8-9-10* | በጣም ብዙ የምሰራው ስራ ስላለ ፀሎት ቅድሚያ የምሰጠው ነገር ነው |
| ለማገልገል የተጠራሁለት ሕዝብ የሚፈልገውን ነገር ለማሟላት ጊዜዬን ሙሉ በሙሉ እነርሱን በማገልገል ላይ እውላለሁ | የሚጠበቁ ነገሮች<br>*1-2-3-4-**5**-6-7-8-9-10* | የሚጠብቁትን ነገር የእግዚአብሔር መንግስት ከሚጠብቀው ነገር ጋር አንድ እንዲያደርጉ ህዝቡን አስተምራለሁ |

## እራስን መመልከት፡-

- የፍፁም ለውጥ እሴት የሆነውን የግል መንግስትን ከማሳደግ የእግዚአብሔር መንግስት ወደማሳደግ መምጣትን በተመለከተ በግል አመለካከታችሁ ልትለውጧቸው ስለሚገቡ ነገሮች እግዚአብሔር ምን እያላችሁ ነው?

- ከግራው ስንጠረዥ ጋር ተጠብቃችሁ እንድትቀሩ የሚያደርጋችሁ ምንድነው? የምን ፍርሀት? ምን ያለፉ ልምምድ?

- በእናንተ እይታ በእውነት ከልቡ የተፀፀተ ሰው ምንን ይመስላል?

## በቤተሰብ ውስጥ በዓርአያነት ማምራት

*በኢየሱስ ክርስቶስ የተለወጠ መሪ ...በቤት ውስጥ እውነተኛ፣ ከልብ የሆነና የአገልጋይነት አመራር የሚያሳይ፣ የትዳር አጋሩን፣ ልጆቹንና የቤተሰቡን አባላት ልክ እንደ ኢየሱስ የሚወድና የሚያገለግል ነው።*

በአንድ ወቅት ከአንድ ከታወቀ ክርስትያን መሪ ጋር ቤተሰብን በዓርአያነት ስለመምራት እየተጨዋወትን ነበር። እንዲህ ነበር ያለኝ: "በዓርአያነት መምራት በቤተሰብ ውስጥ መደረግ የለበትም። ይህን ማድረግ የሚገባን በአገልግሎታችን ውስጥ ብቻ እንጂ በትዳሬም በአባትነት ግንኙነቴ ውስጥ ቦታ የለውም።"

በቡድናችሁ ውስጥ እርስ በእርስ ተጠያየቁ: በዚህ ሰው አስተያየት ትስማማላችሁ ወይስ አትስማሙም? መልሳችሁን አብራሩ።

በእኔ እምነት ለአንድ የወንጌል አገልጋይ በቤተሰብ ውስጥ በአገልጋይነት አመራር ሚና ከመጫወት የበለጠ ቦታ የለውም። አባት ወይም ባል እንዴት በቤተሰቡ ላይ የበላይ ተቆጣጣሪ ስለመሆኑ እያወራሁ አይደለም። እያወራሁ ያለሁት ኢየሱስ የነበረውን አይነት የአገልጋይነት አመራር በቤተሰብ ዓውድ ውስጥ ማራመድ ነው።

ከዚህ ቀጥሎ የሚገኙትን ክፍሎች ድምፃችሁን ከፍ አድርጋችሁ አንብቡና ሰዎች ከርዕሱ ጋር እንዴት እንደሚያዛምዱት ጠይቁ:

መኃልየ መኃልይ 1:6: "የወይን ቦታዎችንም ጠባቂ አደረጉኝ ነገር ግን የእኔን የወይን ቦታ አልጠበቅሁም።


© 2016 MentorLink International

1 ጢሞ 3:4-5: “ልጆቹን በጭምትነት ሁሉ እየገዛ በመልካም የሚያስተዳድር፣ ሰው ግን የራሱን ቤት እንዲያስተዳድር ባያውቅ የእግዚአብሔርን ቤተክርስትያን እንዴት ይጠብቃታል?”

**1. ባሎች እንደ አገልጋይ መሪዎች**

የሚከተሉትን ምንባቦች አንብብ:

- ኤፌሶን 5:23 እና ከ 25-27: “ክርስቶስ ደግሞ የቤተክርስትያን ራስ እንደሆነ እርሱም አካሉን የሚያድን እንደሆነ ባል የሚስት ራስ ነው....ባሎች ሆይ ክርስቶስ ደግሞ ቤተክርስትያንን እንደወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ፤ በውኃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንፅቶ እንዲቀድሳት ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጠ። እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና ያለነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነችን ቤተክርስትያን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ።”

- ቆላስይስ 3:19: “ባሎች ሆይ ሚስቶቻችሁን ውደዱ መራራም አትሁኑባቸው”

- 1 Peter 3:7: “እንዲሁም እናንተ ባሎች ሆይ ደካማ ፍጥረት ስለሆኑ ከሚስቶቻችሁ ጋር በማስተዋል አብራችሁ ኑሩ፤ ፀሎታችሁ እንዳይከለከል አብረው ደግሞ የህይወትን ፀጋ እንደሚወርሱ አድርጋችሁ አክብሩአቸው።”

አሁን ደግሞ በትንሽ ቡድን ሆናችሁ እነዚህን ጥያቄዎች ተወያዩባቸው:

- እግዚአብሔር ባሎች ሚስቶቻቸውን በምን ዓይነት አመለካከት እንዲቀርቧቸው ይናገራል?

- የኢየሱስ የአገልጋይነት አመራር ከዚህ ጋር የሚለያየው እንዴት ነው? ባሎች ክርስቶስ ቤተክርስትያንን እንደወደደ ሚስቶቻችሁን ወደዱ ሲባሉ ተግባራዊ የሆነ ትርጉሙ ምንድን ነው?

- ወደግራ የሚያደሉ መሪዎች ሚስቶቻቸው ላይ ያለቸው ተፅዕኖ ምንድን ነው? ወደቀኝ የሚያደሉስ? ለክርስትያን መሪዎች ከቀኝ ወደግራ መራመድ ማለት በባህላችሁ ምንድን ነው?

- ይህ ሁሉ በባልና በሚስት መካከል ከሚኖር በአርአያነት የመምራት ግንኙነት ጋር ምን ያገናኘዋል?

**2. ሚስቶችና ለባሎቻቸው እንዲሁም ለልጆቻቸው ያላቸው አስተዋፅኦ**

የሚከተሉትን ምንባቦች አንብብ:

- ዘፍጥረት 1:27: “እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ፤ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው።”
- ገላትያ 3:28: “አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፣ ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም፣ ወንድም ሴትም የለም፣ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና።”

አሁን ደግሞ በትንሽ ቡድን ሆናችሁ እነዚህን ጥያቄዎች ተወያዩባቸው:

- በእናንተ ባህል ወንድና ሴት እኩል ቦታ ይሰጣቸዋል? በተለያየ ሁኔታ የሚታዩት እንዴት ነው? በተለያየ ሁኔታ የሚታዩት ለምንድን ነው?

- ለሚከተለው አረፍተ ነገር ምላሽ በመስጠት በትንሽ ቡድን ተወያዩበት: “አንድ ህንዳዊ ክርስትያን መሪ በትልቅ ዓለም ዓቀፍ የመሪዎች ስብሰባ ላይ እንዲህ ብሎ ቃልኪዳን ገባ: ‘በክርስትና አገልግሎት ውስጥ ሚስቴን በብቸኝነት ተጭኜ በአመራር ከፍ ለማለት አልፈልግም።’”
- ከእግዚአብሔር የሆነች ሚስት ባሏን እንዴት ተፅዕኖ ታደርግበታለች? ልጆችዋንስ?

**3. የአባትና የእናት ተፅዕኖ በልጆች ላይ**

የሚከተሉትን ምንባቦች አንብብ:


© 2016 MentorLink International

- ዘዳግም 6:4-9: "እስራኤል ሆይ ስማ፣ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው። አንተም አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹምም ነፍስህ፣ በፍጹምም ኃይልህ ውደድ። እኔም ዛሬ አንተን የማዝዘውን ይህን ቃል በልብህ ያዝ። ለልጆችህም አስተምረው፣ በቤትህም ስትቀመጥ፣ በመንገድም ስትሄድ፣ ስትተኛም፣ ስትነሳም ተጫወተው። በእጅህም ምልክት አድርገህ እሰረው፣ በዓይኖችህ መካከል እንደክታብ ይሁንልህ። በቤትህም መቃኖች በደጃፍህም በሮች ላይ ፃፈው።"

- ምሳሌ 22:6: "ልጅህን በሚሄድበት መንገድ ምራው፣ በሸመገለም ጊዜ ከእርሱ ፈቀቅ አይልም"

- ኤፌሶን 6:4: "እናንተም አባቶች ሆይ ልጆቻችሁን በጌታ ምክርና በተግሣጽ አሳድጓቸው እንጂአታስቆጧቸው።"

አሁን ደግሞ በትንሽ ቡድን ሆናችሁ እነዚህን ጥያቄዎች ተወያዩባቸው።

- የአንድ መጋቢ ልጅ ከአደገ በኋላ እንደዚህ አይነት አስተያየት ተናገረ: "አንዳንድ ጊዜ አባቴ በእውነት ስለኔ ሳይሆን የሚያስበው ስለራሱ ስም ነው ብዬ አስባለሁ።" ይህ ወጣት ለማለት የፈለገው ምንድን ነው? ይህ እንደእናትና እንደአባት ምን አይነት ተፅዕኖ አድራጊ እንድንሆን ያደርገናል?

- ወደግራ የሚያደሉ መሪዎች ልጆቻቸው ላይ ያላቸው ተፅዕኖ ምንድን ነው? ወደቀኝ የሚያደሉስ? ለክርስትያን ቤተሰብ ከቀኝ ወደግራ መራመድ ማለት በባህላችሁ ምንድን ነው ?

- ይህ ሁሉ በባልና በሚስት መካከል ከሚኖር ልጆችን በአርአያነት የመምራት ግንኙነት ጋር ምን ያገናኘዋል? ትልልቅ ልጆችን እና ትንንሾችን በአርአያነት ለመምራት የአቀባበል ልዩነትን ግምት ውስጥ አስገባ።

**መደምደሚያ**

ከዚህ ክፍለ ጊዜ የምትወስደው ዋና መልዕክት እና ተግባር ምንድን ነው? ከዚህ በታች መዝግባቸው:

1)

2)

3)


© 2016 MentorLink International

## የእሴት ለውጥ #2፡የፀጋ አገልግሎት

### በመቆጣጠር ላይ ከተመረኮዘ መሪነት ወደ ጸጋ መሪነት

« . . . የመንፈስ ህብረት ቢሆን፣ ምህረትና ርህራሄ ቢሆን፣ ደስታዬን ፈጽሙልኝ፣ በአንድ ሀሳብ ተስማሙ አንድ ፍቅር አንድም ልብ አንድም አሳብ ይሁንላችሁ፤ ለወገኔ ይጠቅማል በማለት ወይም በከንቱ ውዳሴ ምክንያት አንድ እንኳ አታድርጉ ነገር ግን እያንዳንዱ ባልንጀራው ከራሱ ይልቅ እንዲሻል በትህትና ይቁጠር እያንዳንዱ ለራሱ የሚጠቅመውን አይመልከት ለባልንጀራው ደግሞ እንጂ» ፊሊጵስዩስ 2፣2-4

በክርስቶስ ኢየሱስ ፍጹም የተቀየረ መሪ . . . በግሉ በሚጨምር ሀይልና አስገራሚ ፀጋ የተያዘ ነው መዋረድንና ምህረትን ተለማምዷል፡፡ በተጨማሪም ሌሎችን በተመሳሳይ አቀባበል ምህረትና ፍቅር የሚቀበል ነው፡፡

### ሕጋዊነት ወይም በቁጥጥር ላይ የተመሰረተ መሪነት ሌሎችን እንዴት ነው የሚይዛቸው?

ማቴ23፡23-28ን አንብቡ፡፡ በዚህ ክፍል ኢየሱስ በፍጹም ለውጥ እሴቶች አንፃር «የግራዉ በኩል መሪዎች» ተብለው ሊጠሩ ስለሚችሉት የእስራኤል ሃይማኖታዊ መሪዎች ይናገራል በተጨማሪም ለእነርሱ በቀጥታ ይናገራል፡፡

1. ኢየሱስ ለሕጋዊነት የሰጠው ምላሽ ምን እንደሆነ ከዚህ ቁጥር በመመልከት ግለጹ፣ በጣም ግልፅ ሁኑ

2. በዚህ ቁጥር መሰረት የህጋዊ መሪነት ውጤቶቹ ምን ምን ናቸው?

3. ለምን ወይም እንዴት መሪዎች ህጋዊ ይሆናሉ?

### ፀጋ ሌሎችን እንዴት ነው የሚይዘው?

ከፈሪሳዊያን ጋር በማነጻጸር ከዚህ በታች ባሉት ጥናታዊ መረጃዎች የ«ቀኝ ረድፍ» መሪ እራሱን እንደማያከብር ሌሎችን እንደማይቆጣጠርና እንደማያታልል . . . ወይም ስለመልካም ስነምግባር እርግት እንደማያሳይ ተመልከቱ፡፡ ይልቅ የሚታየውን ፀጋ ቸርነት እንዲሁም ርህራሄ ተመልከቱ፡፡ ሉቃ 7፡36-50ን አንብቡ፡፡

1. ኢየሱስ ለዚህች ሀጢያተኛ ሴት በፀጋው እንዲደርስላት የሳቡት ነገሮች ምንድናቸው?

2. የ “ግራ ረድፍ” ሀይማኖታዊ መሪው ስምኦን ለኢየሱስና ለፀጋው እንዴት ነው ምላሽ የሰጠው?

3. የዚህች ሴት ያለፈው የሕይወቷ ክፍል ከኢየሱስ ጋር የነበራትን ግንኙነት በምን አይነት ሁኔታ ነው ተጽእኖ ያሳደረበት?


© 2016 MentorLink International

## ራስን ዝቅ ማድረግና አገልግሎት

ራስን ዝቅ ማድረግ የእግዚአብሔርን ፀጋ ስፋት እንድንረዳ መሰረታዊ አስተዋጾ ያበረክታል፡፡ ከክብራችን ከዝናችን ለራሳችን ካለን ግምት እንዲሁም ከስልጣናችንና ከተቆጣጣሪነታችን ዝቅ ስንል ብቻ ነው ሌሎችን በፀጋ መንከባከብ የምንችለው፡፡

በ (ሉቃ 15፡11-32) የሚገኘውን የአባካኙን ልጅ ምሳሌ አስቡ በተጨማሪም የአባትየው ልብ ከዚህ በታች ባለው መሰረት ልጆቹን ከግራ ወደ ቀኝ እንዳቀያየረ አድርጋችሁ አስቡ፡፡

| ታላቁ ልጅ | ታናሹ ልጅ |
|---|---|
| • ይሰማል<br>• ኩሩ ነው<br>• ግትር<br>• ባለሙብት ነበር<br>• አባቱን ከርቀት ነው የሚያውቀው<br>• ህግ<br>• ስራ ላይ ያተኮረ ነው<br>• የጠፋ<br>• የሞተ<br>• ትክክል ግን የተሳሳተ<br>• ይቃወማል | • ያደምጣል<br>• ጭምት<br>• የተሰበረ ልብ<br>• ታቀፈ<br>• አባቱን በቅርበት ያውቀዋል<br>• ፍቅር<br>• ግንኙነት ላይ ያተኮረ<br>• የተገኘ<br>• በሕይወት ያለ<br>• የተሳሳተ ግን ትክክል የሚፀፀት |

በተጨማሪም ጳውሎስ በመንፈሳዊ ብስለት በአገልግሎት ውጤታማነትና ከክርስቶስ ጋር በአንድነት እያደገ በነበረበት ጊዜ እንኳን ለራሱ የነበረውን አመለካከት ተመልከቱ፡፡ በጊዜ ቅደም ተከተል ጳውሎስ ስለራሱ እንደዚህ ብሏል፡-

1. በ49 ዓ.ም- ከሌሎች ሀዋርያት ጋር እኩል (ገላ1፡16 ፤ 2፡10)
2. በ53ዓ.ም- በሀዋርያት መሀከል የሁሉ የበታች ( 1ቆሮ 15፡9)
3. በ61ዓ.ም- ከእግዚአብሔር ሰዎች መሀከል የሁሉ የበታች (ኤፌ 3፡8)
4. በ65 ዓ.ም- የሀጢያተኞች አለቃ (1ጢሞ 1፡15)

በጳውሎስ ሕይወት ውስጥ የነበረውን እድገትና እግዚአብሔር በየቀኑ የበለጠ ጭምት እንዲሆን እያደረገ እንዴት እንደቀየረው በድጋሚ ተመልከቱ፡፡ በጳውሎስ ሕይወት ውስጥ ወደ ሚያድግ ራስን ዝቅ ማድረግ የመራ ምን የተከሰተ ነገር ያለ ይመስለችኋል?

ራስን ዝቅ ማድረግ እኛ የምናደርገው ነገር ሳይሆን እግዚአብሔር በሚያደርገው የሕይወት ሂደቶች ውስጥ ወደኛ የሚመጣ ነገር ነው፡፡ ራስን ዝቅ ማድረግ ለእነዚህ የህይወት ሂደቶች በምንሰጠው ምላሽ ሊከሰትም ላይከሰትም ይችላል፡፡ እግዚአብሔር እኛን ከግራ በኩል መሪነት ወደ ቀኝ በኩል መሪነት እንዲያመጣን ራስን ዝቅ ማድረግ መሳሪያ ሆኖ የሚያገለግለው እንዴት ነው?

## በፀጋ የማገልገልን የእሴት ለውጥ . . . . የቅርብ እይታ ማድረግ

### በትንሽ ቡድናችሁ በዚህ የአመለካከት ለውጥ ዙሪያ ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች ተወያዩባቸው፡፡

1. ይህ የአመለካከት ለውጥ በአጠቃላይ ስለ ምንድነው? በራሳችሁ ቃል ግለጹ

2. ይህንን የአመለካከት ለውጥ በተመለከተ በሀገራችሁ ስላለው የመሪነት ባህል የግል አስተያየታችሁ ምንድነው?


© 2016 MentorLink International

## የለውጥ እሴት #2 የግል ግምገማ

ከዚህ በታች ባለው የለውጥ እሴት ባስተሳሰባችሁ እንዲሁም በልምምዶቻችሁ የቱ ጋር እንዳላችሁ ገምግሙ፡፡ በመሀከለኛው ክፍል ላይ ካሉት ቁጥሮች እናንተ በተሰጡት መንታ ሀሳቦች አኳያ የቱ ጋር እንዳላችሁ በማክበብ አሳዩ፡፡ ለምሳሌ በስተግራ ባለው ሰንጠረዥ ውስጥ ያለው ሀሳብ ያብዛኛውን ጊዜ ማንነታችሁን የሚገልጽ ከሆነ ለራሳችሁ «1» ስጡ በቀኝ ያለው ከሆነ ደግሞ «10» ስጡ በመሀከል ካላችሁ «5» ስጡ በተጨማሪም ከዚህ በታች ላሉት እራስን መገምገሚያ ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡

| በመቆጣጠር የመምራት አካሄድ | ... ወደ... | በፀጋ የመምራት ሂደት |
|---|---|---|
| እግዚአብሔር ውጤታማ የሆነ ስራን ይፈልጋል። እሩቅ የማይገኝ ለማስደሰት ከባድ የሆነ እንደሆነ ነው የሚሰማኝ፡፡ | የእግዚአብሔር እይታ<br>1-2-3-4-5-6-7-8-9-10 | እግዚአብሔር የሚወደኝ አባቴ ነው እኔን ለማዳንና የግሉ ለማድረግ ልጁ በሞት እንዲሰቃይ ያደረገ አባቴ ነው፡፡ |
| የሕይወት ዕድገት ለማምጣት ቁልፉ እግዚአብሔርን ለማስደሰት በይበልጥ መጣር | እድገት<br>1-2-3-4-5-6-7-8-9-10 | እውነተኛ ለሆነ መለወጥ ቁልፉ ከስላሴዎች ጋር የጠለቀ ግንኙነት መፍጠር ነው፡፡ |
| ሁልጊዜም በእግዚአብሔር ፊት የጥፋተኝነት ስሜት ይሰማኛል፡፡ | ምህረት<br>1-2-3-4-5-6-7-8-9-10 | ሁልጊዜም በአምላኬና በአዳኙ ምህረት እንደተደረገልኝና እንደተወደድኩ ይሰማኛል፡፡ |
| የቅድስና ኑሮ የሚገለጠው እግዚአብሔርን ለመታዘዝ በማደርገው ቋሚ ትጋት ነው | በቅድስና መኖር<br>1-2-3-4-5-6-7-8-9-10 | ቅድስና አስፈላጊ ነው፡፡ በቅድስና መኖር የሚቻለው ከእግዚአብሔር ጋር በቅርበት መራመድ ስጀምር ነው |
| የምመራው በሀፍረትና በጥፋተኝነት ስሜት ነው | ሀፍረትና ማንነት<br>1-2-3-4-5-6-7-8-9-10 | በእግዚአብሔር የተወደድኩ ልጁ እንደሆንኩ አውቃለሁ |
| እንደ ክርስቲያን በትክክል ህይወት ጉዞ ለመቀጠል ህግጋትን መከተል ያስፈልገናል | ደንቦች/ህግጋት<br>1-2-3-4-5-6-7-8-9-10 | ያለማቋረጥ ወደ መስቀሉ እንዲያመጡን የሰው ሳይሆን የእግዚአብሔር ሕግጋት ያስፈልገናል |
| መንፈስ ቅዱስ ማን እንደሆነና በእርሱም መገናኘት እንዴት መመላለስ እንዳለብኝ ምንም አይነት ተግባራዊ መረዳት የለኝም፡፡ | መንፈስ ቅዱስ<br>1-2-3-4-5-6-7-8-9-10 | በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ከእግዚአብሔር ጋር የቀረበ ግንኙነት መፍጠር እየተማርኩ ነው፡፡ |
| እውነቱን ለመናገር በተሰጡኝ ስጦታዎች ችሎታዎች እንዲሁም ባገኘኋቸው ውጤቶች በጣም እኩራራለሁ፡፡ | ኩራቴ #1<br>1-2-3-4-5-6-7-8-9-10 | ኢየሱስ እንደኔ ያሉትን የቤተሰቡ አካል ለማድረግ በከፈለው ዋጋ እደሰታለሁ |
| ከሌሎች ጋር ሲነፃፀር አብዛኛውን ጊዜ በስጦታዎቼ ችሎታዎቼ እንዲሁም ባገኘኋቸው ውጤቶች አፍራለሁ፡፡ | ኩራቴ #2<br>1-2-3-4-5-6-7-8-9-10 | የተወደደ ልጁ እንደመሆኔ መጠን ክርስቶስ በእኔና እኔን ተጠቅሞ በእምነት በሚሰራው ስራ ብቻ መኩራት እንደለብኝ እየተማርኩ ነው፡፡ |
| <u>ውጤታማ</u> የሆነ አገልግሎት የሚገኘው ከራሴ ጥንካሬ በሆነ አገልግሎትና አመራር ነው፡፡ | ራስን ዝቅ ማድረግ<br>1-2-3-4-5-6-7-8-9-10 | <u>ውጤታማ</u> የሆነ አገልግሎት አብዛኛውን ጊዜ የሚከናወነው በድካሜ ራስን ዝቅ በማድረግና በግልጽ ሳገለግል ነው |
| ፀሎት እግዚአብሔርን ለማስደሰት ማድረግ እንዳለብኝ የሚሰማኝ ስርዐት ነው፡፡ | ለፀሎት ያለን አመለካከት<br>1-2-3-4-5-6-7-8-9-10 | ፀሎት ደስታ ነው፣ መንፈስ ቅድስ ከአባቴና ከልጁ ጋር በፍቅራዊ ህብረት እንድገናኝ ሚደረግበት የተሰጠኝ ነው፡፡ |

### እራስን መመልከት፡-

- የለውጥ እሴት የሆነውን የግል መንግስትን ከማሳደግ የእግዚአብሔርን መንግስት ወደማሳደግ መምጣትን በተመለከተ በግል ግምገማችሁ ልትለውጧቸው ስለሚገቡ ነገሮች እግዚአብሔር ምን እያላችሁ ነው?
- በግራው ሰንጠረዥ ላይ መልህቅ እንድትጥሉ ያደረጋችሁ ምንድነው?ምን አይነት ስጋት? ምን አይነት ልምምዶች?


© 2016 MentorLink International

- በእናንተ እይታ በእውነት ከልቡ የተፀፀተ ሰው ምንን ይመስላል?

## የእሴት ለውጥ #3፡አገልጋይ መሪነት

### ስልጣንና መሰረት ካደረገ መሪነት ወደ አገልጋይ መሪነት

«. . . ነገር ግን ማንም ከእናንተ ታላቅ ሊሆን የሚወድ የእናንተ አገልጋይ ይሁን ከእናንተም ማንም ፊተኛ ሊሆን የሚወድ የእናንተ ባሪያ ይሁን፡፡ እንዲሁም የሰው ልጅ ሊያገለግል ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም፡ ማቴ 20፡26-28

በኢየሱስ ክርስቶስ እየተቀየረ ያለ መሪ . . . ተጽእኖው ወይም አሻራውን የሚያሳድረው በስልጣን ወይንም በሀይል አይደለም ነገር ግን ሌሎችን በክርስቶስ ትህትና በማገልገል ተጽእኖን ያሳድራል፡፡

## ኢየሱስ በዛን ጊዜ የነበረውንና በአሁን ጊዜ ያለውን የሀይል አመራር ይነቅፋል

ኢየሱስ ለመንቀፍ የተናገራቸው ቃላት በጊዜው የነበሩት መሪዎችና አስተማሪዎች ላይ በቀጥታ ያተኮሩ ነበሩ፡፡ እንደ መንፈሳዊ መሪነታችን ኢየሱስ እዚህ ጋር ያለውንና በሀይል ስለሚመሩ መሪዎች ለሚሰማውን ነገር ትኩረት መስጠታችን እጅጉን አስፈላጊ ነው፡፡

ማቴ 23፡1-12 ን በማንበብ ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡

- ይህንን ክፍል ስታነቡ በክርስቶስ ዘመን የነበሩትን መንፈሳዊ መሪዎችን በተመለከተ የኢየሱስ አንድ ወይም ሁለት ነቀፋዎች ውስጥ ለእናንተ የሆነውን ግለጹ? መልሳችሁን አብራሩ፡፡
- ኢየሱስ እንዳየው ፈሪሳውያንን እንደ መሪዎችን የሚያንቀሳቅሱ መሰረታዊ አነሳሾች ምን ምን ናቸው? (ቁጥር 5-7)
- አሁን ባላችሁበት ባህል በሀይል የሚመሩ መሪዎች ተመሳሳይ አመለካከቶችንና ባህሪዎችን እንዴት ነው የሚያንፀባርቁት?
- በመጨረሻ ኢየሱስ በቁጥር 12 ላይ ለመሪዎች የገባውን ቃል ኪዳን ተመልከቱ፡፡ እነዚህ ሁለት ቃል ኪዳኖች ምን ምን ናቸው? ይሄስ ለእናንተ ምን ማለት ነው?

## በሀይል ተጠቅሞ ከመምራት መሪነት ወደ በአገልጋይነት ባህሪ መምራት ለሚደረገው ሂደት የሚያገለግል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥናት፤ ያዕቆብ፣ ኢየሱስ፣ እንዲሁም ዮሐንስ

ያዕቆብና ዮሐንስ በኢየሱስ ተመርጠው በአገልግሎቱ ውስጥ የተለየ ቦታ ተሰጥቷቸው ነበር፡፡ ነገር ግን ይህ ማለት ማበረታታት እና እርማት ከአምላካቸውና ከመምህራቸው ከክርስቶስ ኢየሱስ ከዚህ በኋላ አያስፈልጋቸውም ነበር ማለት አይደለም፡፡

ማርቆስ10፡35-45ን በማንበብ ኢየሱስ ያዕቆብንና ዮሐንስን ሥጋዊ አመራርን በመተው እንደ መሪ እርሱን እንዲመስሉ ለማድረግ እንዴት እንደሞከረ ተመልከቱ፡፡ ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡

- ያዕቆብና ዮሐንስ ከኢየሱስ እየጠየቁ የነበረው ነገር ምን ነበር?ይህንን ጥያቄ ለምን ያቀረቡ ይመስላችኋል? (ቁጥር 35-37)


© 2016 MentorLink International

- ኢየሱስ «. . . የምትጠይቁትን አታውቁም . . .» ብሎ ሲመልስላቸው ምን ለማለት ፈልጎ ይመስላችኋል (ቁጥር 38) ? በቁጥር 40 ላይ ያለው የኢየሱስ ጠንካራ ግሳጼ የያዕቆብና የዮሐንስን የአገልጋይ መሪነት ብቃት ገድቦታል? ለምን?

- ሌሎቹ የያዕቆብና የዮሐንስን ጥያቄ ሲሰሙ ተናደዱ፤ በዚህ መንገድ የተንቀሳቀሱት ለምን ይመስላችኋል? (ቁጥር 41)?

- ባላችሁበት ቤተክርስትያን ያሉት መንፈሳዊ መሪዎች የአገልጋይ መሪነትን እሴቶችን እንዲይዙና ኢየሱስ በዚህ ክፍል ከቁጥር 42-45 ከእኛ የጠየቃቸውን ነገሮች እንዲለማመዱ ቢያስፈልግ ምን ለውጦች መካሄድ አለባቸው? በተጨማሪም ባላችሁበት ቤተክርስቲያን እናንተንና ሌሎች መሪዎች በዚህ ክፍል ያለውን የኢየሱስን ቃል ብትታዘዙ ምን ለውጥ የሚመጣ ይመስላችኋል?

## እንደ አገልጋይ መሪነታችን የኢየሱስን ፈለግ የምንከተልበት መንገዶች

በትንንሽ ቡድቻችሁ ከዚህ በታች ያሉትን ሃሳቦች ከፍ ባለ ድምጽ አንብቡ። ስለአንድ አንድ በአርአያነት የሚመራ ሰው አአዕምሮአችሁ አስቡ፣ በተጨማሪም ለእያንዳንዱ ዓረፍተ ነገር አንድ ወይም ሁለት ተግባራዊ ምሳሌዎች አስቡ፡

- **የሌሎችን እውነተኛ ፍላጎት እናሟላለን** የእግዚአብሔር ፀጋ ፍቅር እንዲሁም እውነት ላይ ያላቸውን መረዳትና ልምምድ በሚያጠናክር መልኩ፡፡

- **ሰዎችና በመልካም ግንኙነት ላይ እናተኩራለን፡፡** ስራው መሰራት እንዳለበት እናውቃለን፡፡ ነገር ግን ከፍተኛውን ሀይላችንን ሌሎች የምንመራቸውን በመንከባከብና ጠንካራ ግንኙነቶች በመፍጠር ላይ እናውለዋለን፡፡

- **ሌሎችን እንቀርባቸዋለን** በሀይል፣ በመፈታተን ወይም በቁጥጥር ሳይሆን በትህትናና በፍቅር፡፡

- **ስልጣናችንን የተሰጠንን ቦታ በመስዋዕትነት ሌሎችን ለማገልገል እንጠቀማለን፡፡** በህይወታቸውና በአገልግሎታቸው በውጤታማነት እንዲወጡ ለማስታጠቅ

- **ዕውቅናንና ሽልማትን ሳንጠይቅ እናገለግላለን** በእግዚአብሔር ፍቅርና ጥሪ በመታቀፍ የእርሱን ተቀባይነት እንጂ የሌሎችን ሳንፈልግ እናገለግላለን፡፡

## የአገልጋይ አመራር እሴት ለውጥ . . . የቅርብ እይታ

**በትንሽ ቡድናችሁ በዚህ የአመለካከት ለውጥ ዙሪያ ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች ተወያዩባቸው፡፡**

1. ይህ የአመለካከት ለውጥ በአጠቃላይ ስለምንድነው? በራሳችሁ ቃል ግለጹ፡፡

2. ይህንን የአመለካከት ለውጥ በተመለከተ በሀገራችሁ ስላለው የመሪነት ባህል የግል አስተያየታችሁ ምንድነው ?


© 2016 MentorLink International

# የፍጹም ለውጥ እሴት #3 የግል ግምገማ

*ከዚህ በታች ባለው የፍጹም ለውጥ እሴት ባስተሳሰባችሁ ባመለከታችሁ እንዲሁም በልምምዶቻችሁ የቱ ጋር እንዳላችሁ ገምግሙ:: በመሐከለኛው ከፍል ላይ ካሉት ቁጥሮች ለእናንተ በተሰጡት መንታ ሀሳቦች አኳያ የቱ ጋር እንዳላችሁ በማክበብ አሳዩ:: ለምሳሌ በስተግራ ባለው ሰንጠረዥ ውስጥ ያለው ሀሳብ ያብዛኛውን ጊዜ ማንነታችሁን የሚገልጽ ከሆነ ለራሳችሁ «1» ስጡ በቀኝ ያለው ከሆነ ደግሞ «10» ስጡ በመሀከል ካላችሁ «5» ስጡ በተጨማሪም ከዚህ በታች ላሉት እራስን መገምገሚያ ጥያቄዎች መልስ ስጡ::*

| በስልጣን ላይ የተመሰረተ አመራር | ... ወደ... | የአገልጋይነት አመራር |
|---|---|---|
| ከሌሎች ጋር በሚኖረኝ አገልግሎት ከግንኙነት ይልቅ ለተሰጠኝ ሥራ ቅድሚያ እሰጣለሁ:: | ግንኙነት ከሥራ ጋር ሲነፃፀር<br>*1-2-3-4-5-6-7-8-9-10* | በአገልግሎት ውስጥ ግንኙነትም ስራም አስፈላጊ ነገሮች ናቸው:: እንደ እግዚአብሔር ሰዎች አንድነታችን ለውጤታችን ቁልፍ ነው:: |
| የመሪነት ስልጣኔን በዋነኛነት ከተሰጠኝ የስራ ዝርዝር ስልጣንና የድርጅታችን የሥልጣን ተዋረድ ውስጥ እወስዳለሁ | ***ስልጣን***<br>*1-2-3-4-5-6-7-8-9-10* | ስልጣኔ በዋነኛነት የሚመሰረተው መተማመን ግንኙነት አንድነት እንዲሁም አገልግሎት ላይ በተመረኮዘ መንፈሳዊ ስልጣን ላይ ነው:: |
| ከበሬታ ከያዝኩት ስልጣንና ቦታ ጋር አብሮ የሚመጣ ነው:: | ***አክብሮት***<br>*1-2-3-4-5-6-7-8-9-10* | ከበሬታ በዋነኛነት ክርስቶስን አላማውን እንዲሁም ሕዝቡን ሳገለግል የሚመጣ ነገር ነው |
| ቡድናችን ጥሩ እንዲሰራ በመምራት ለሰራሁት ስራ የሚገባኝን ከበሬታ ማግኘት እጠብቃለሁ። ስኬት የምለው ይህንን ነው። | ***የአመራር ስኬት***<br>*1-2-3-4-5-6-7-8-9-10* | ስኬት የሚመጣው የቡድን አባላቶቼን በማስታጠቅና በማበረታታት ነው:: ከዚህ የተነሳ የእርሱን ሥራ ለእርሱ ክብር እናከናውናለን:: |
| እንደ መሪ ስኬትን ለማግኘት እንዳስፈላጊነቱ ሰዎችን በመጠቀም የሥራችንን እያንዳንዱን ነገር በቀጥተኛ መንገድ እቆጣጠራለሁ:: | ***ቁጥጥር 1***<br>*1-2-3-4-5-6-7-8-9-10* | ተቆጣጣሪው እግዚአብሔር ነው:: የድርሻቸውን ለመሥራት የታመኑ የእምነት ሰዎችን በማሳደግና በመርዳት ከእነርሱ ጋር እሰራለሁ:: |
| በድርጅት አባላት መሐከል በሚደረጉ ግንኙነቶች በተጨማሪም በጣም አስፈላጊ በሆኑ ውሳኔ አሰጣጦች ሁሉ ላይ መሳተፍ እፈልጋለሁ:: | ***ቁጥጥር 2***<br>*1-2-3-4-5-6-7-8-9-10* | የታመኑ የቡድን አባላት እንደ ቡድን ያሰፈርነውን እቅድ መስመር ተከትለው በነፃነት እንዲሰሩ ውሳኔ መስጠት እንዲችሉ አደርጋለሁ |
| በስራ ቡድናችን ውስጥ የውጪ ሰዎችን ጨምሮ ሁሉም ሰው መሪው እኔ እንደሆንኩ እንዲያውቅ አደርጋለሁ | የመሪ ማንነት<br>*1-2-3-4-5-6-7-8-9-10* | ከውጭ ሆኖ የሚመለከት ሰው መሪው እኔ እንደሆንኩ በቀላሉ ላያውቅ ይችላል:: በማንኛውም የአገልግሎት አቅጣጫ ስጦታን የተመረኮዘ የህብረት መሪነት እንለማመዳለን:: |
| እንደ መሪ የምመራቸውን ሰዎች በተቻለ መጠን ደስተኛ እንዲሆኑ በማድረግ ተጽእኖ ማሳደር ስራዬ ነው | ሰዎችን ማስደሰት<br>*1-2-3-4-5-6-7-8-9-10* | ክርስቶስን፣ የመንግስቱን አላማና ህዝቡን ሳገለግል አንዳንዴ አንዳንድ ጓደኞቼን ላያስደስቱ የሚችሉ ከባድ ውሳኔዎችን መወሰን ይኖርብኛል |
| በእኔ አመራር ስር ካሉት ጋርና ስላሉት በመፀለይ በጣም ጥቂት ጊዜ ብቻ ነው የማጠፋው:: | በፀሎት አመራር<br>*1-2-3-4-5-6-7-8-9-10* | ለምመራቸውና ከምመራቸው ጋር ሁልጊዜ እፀልያለሁ ምክንያቱም ስለሚያበረታታቸውና ሀይል ስለሚሆናቸው ነው |

## *እራስን መመልከት*

- የለውጥ እሴት የሆነውን የግል መንግስትን ከማሳደግ የእግዚብሔርን መንግስት ወደማሳደግ መምጣትን በተመለከተ በግል አመለካከታችሁ ልትለውጧቸው ስለሚገቡ ነገሮች እግዚአብሔር ምን እያላችሁ ነው?
- ከግራው ሰንጠረዥ ጋር ተጠብቃችሁ እንድትቀሩ ያደረጋችሁ ምንድነው? የምን ፍርሃት? ምን ያለፉ ልምምዶች?
- በእናንተ እይታ በእውነት ከልቡ የተናዘዘ ሰው ምንን ይመስላል?


© 2016 MentorLink International

## የእሴት ለውጥ #4: ትብብር እና ማህበረሰብ

### ከ አምባገነንነና እኔ እበቃለሁ ባይነት ወደ ትብብርና ህብረት

ስለ ክርስቶስ ወንጌል ወደ ጢሮአዳ በመጣሁ ጊዜ ለጌታ ሥራ በር ምንም ቢከፍትልኝ ቲቶን ወንድሜን ስላላገኘሁት መንፈሴ ዕረፍት አልነበረውም ስለዚህ ከእነሱ ተሰናብቼ ወደ ሜቄዶንያ መጣሁ፡፡

2 ቆሮ 2፡12-13

በክርስቶስ እየሱስ ፍጹም እየተቀየረ ያለ መሪ...ከኩራት ወይም ለማካፈል ፈቃደኛ ካልሆነ ህይወት የተነሳ ከሚመጣ ብቸኝነትና ተነጥሎ የመስራት ፍላጎት እራሱን የሚከላከል ነው፡፡ ይህ መሪ ከሌሎች ጋር የሚኖረውን ግንኙነት ትልቅ ቦታ ይሰጠዋል በተጨማሪም እርሱ ደካማ በሆነበት ጎን ጠንካራ ከሆኑ ሰዎች ጋር ይሰራል

**ብዙውን ጊዜ የቡድን አመራር ከግል አመራር እጅግ ፈታኝ ነው**

ማገናኛችንም በሁሉም አቅጣጫ ብቁዎች አይደለም፡፡ አንዳችን ለአንዳችን እንጠቅማለን። ቢሆንም ግንኙነታችን ብዙ ስራ ያስፈልገዋል እናም አንዳንድ ጊዜ በግላችን ከመስራት ይልቅ በቡድን መስራት ጊዜ የሚፈጅና ፈታኝ ነው።የተመረጠው መንገድ የቡድን መሪነት ከሆነ እነዚህ ፈተናዎች የማይቀሩ ናቸው፡፡ አንዳችን ላንዳችን በፀጋና በፍቅር ለማደግና የበለጠ ፍሬያማ ለመሆን የሚረዱን መንስኤዎች አድርገን እነዚህን «ፈተናዎች» መያዝን መማር ይኖርብናል፡፡

- በብቸኝነት እራሱን የቻለ መሪ ሆኖ ከመስራት ጋር የሚዛመዱ ችግሮች ምን ምን ናቸው?

- በቡድን የመምራት መልካም ጎኖች ምን ምን ናቸው?

**ክርስቶስን ማዕከል ያደረገ መሪ ትብብርና ህብረትን ትልቅ እሴቶቹ ያደረገ ሰው ነው፡**

- የአምላክ አንድነት ልዩነት እንዲሁም በጋራ መስራት በስላሴዎች እንደሚታየው በመሪዎች ቡድን መካከል የሚታየው እኩልነትና መከባበር ለእግዚአብሔር ሀይልና መገኘት ትልቅ ምስክር ነው

- በብሉይ ኪዳን መልካም የመሪነት ምሳሌ የሆኑት "ታላላቅ ሰዎች" (ነብያትና ነገስታት) ራሳቸውን በእግዚአብሔር የተቀቡ ባደረጉ በዛሬው ዘመን መሪዎች ወደተበላሸ የአመራር ልምምድ እየተወሰደ ነው፡፡

- ብቸኛ መሪ የሚለው ሀሳብ ለአዲስ ኪዳን ባዕድ ነገር ነው። ክርስቶስን ማዕከል ያደረጉ መሪዎች ከቡድኑ አባለት ጋር እኩል አስተዋፅኦ ያደርጋሉ። በአዲስ ኪዳን ውስጥ አልፎ አልፎ የመጨራሻ ውሳኔውን አንድ ሰው ብቻ የሚያደርግበትን ሁኔታ እናገኛለን፤ ነገር ግን በአብዛኛው በቡድን የሆኑ መሪዎችን ነው የምናገኘው

- በመንፈሳዊ መንገድ ፍጹም የተቀየረ መሪ ጥንካሬውንና ድክመቱን ይገነዘባል በተጨማሪም የእርሱን ድክመት ሊሸፍን የሚችል ጥንካሬ ካላቸው ሰዎች ጋር ለመስራት ይፈልጋል ሁሉንም ነገር በደንብ አለመቻሉን ለማመን ሀፍረት አይሰማውም፡፡

እነዚህን ቁልፍ ሀሳቦች ከሰማችሁ በኋላ አስተያየታችሁን ስጡ፡፡ በሰማችሁት ሀሳብ ላይ ትስማማላችሁ? እነዚህ ሀሳቦች አስተሳሰባችሁን እንዴት ነው ያነቃቁት?


© 2016 MentorLink International

## በቡድን አመራርና ትብብር ዙሪያ ጥቂት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌዎች

ከዚህ በታች ያሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በማንበብ በቡድናችሁ ተወያዩባቸው

- **ደቀመዛሙርት** (ሉቃ 10፡1-2፤17፤21) ጌታ ኢየሱስ 72ቱን ደቀመዛሙርት ሀላፊነት ሰጥቶ ሲልካቸው አንድ በአንድ ቢሔዱ ኖሮ ሁለት እጥፍ የሚሆን አካባቢ መሸፈን ይችሉ ነበር፡፡ ነገር ግን 36 ጥንዶች አድርጎ ላካቸው። ሲመለሱ ስለ መስክ ልምምዳቸው ምን ሪፖርት ይዘው ነው የተመለሱት? የሚሰማቸው ስሜት እንዴት ነበር? ስለዚህ ተልእኳቸው ኢየሱስ ከመለሰው መልስ ምን ተሰምቶት እንደነበር እንገምታለን? ለብቻ ከመስራት ይልቅ በጋራ ስለመስራት ምንን አስተማረ?

- **ኢየሱስ** (ማር 14፡32-34) ኢየሱስ ሲፀልይ ብቻውን ይሆን ነበር፤ ነገር ግን በጌቴሴማኒ በይሁዳ አልፎ በተሰጠበት ምሽት ይህ አልሆነም፡፡ ኢየሱስ ከጴጥሮስ ከያዕቆብ እንዲሁም ከዮሐንስ ይፈልገው የነበረ እርዳታ ምን ነበር? የእግዚአብሐር ልጅ በዚህ መንገድ እርዳታን መፈለጉ አስገርሟችኋል? ለምን?

- **በርናባስ** (የሐዋ 11፡19-27) በርናባስ በአንጾኪያ ብዙ የሚሰራ ስራ እንዳለ ሲመለከት በራሱ ሁሉንም ለስራት መሞከር ይችል ነበር ነገር ግን አላደረገውም፡፡ እርዳታ ለማግኘት ከራሱ መንገድ እንዴት ዞር አለ? በመረጣቸው ረዳቶች ምን አይነት ሀላፊነት ነው የወሰደው? የዚህ የቡድን አገልግሎት ውጤቱ ምን ነበር?

- **ጳውሎስ** (2ጢሞ 4፡9-13፤19-21) ጳውሎስ በኩራትና በመልካም ሁኔታ አገልግሎቶን ጀመረ ነገር ግን ተለወጠ፡፡ በእነዚህ ሁለት ክፍሎች ምን ያህል ጓደኞቹንና ተባባሪ ሰራተኞችን ጠቅሷል? ጳውሎስ የህብረት ሥራን መንገድ ባይከተል ኖሮ ውጤታማ የሆነውን ያህል ውጤታማ የሚሆን ይመስላችኋል? ለምን?

## የኢየሩሳሌም ምክር ቤት፡ የቡድን አመራር ምሳሌያዊ ጥናት

የሐ/ሥራ 15፡1-29ን በማንበብ ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች ተወያዩባቸው፡፡

- በዚህ ምንባብ ውስጥ የግራ በኩል መሪዎች እነማን ነበሩ ? ፍላጎታቸው ምን ነበር ?
- በእየሩሳሌም ተሰብስበው የነበሩት የግራ በኩል ሐዋርያትና ሽማግሌዎች ስራዎቻቸውና ሃላፊነቶቻቸው ምን ነበሩ?

- ጴጥሮስ፣ በርናባስ፣ ጳውሎስ እንዲሁም ያዕቆብ በስብሰባው ወቅት ምን አይነት አስተዋጽኦ አበርክተዋል? ከእነዚህ ሰዎች ውስጥ የስብሰባውን የመጨረሻ ንግግር ያቀረበ አለ?

- የምክር ቤቱ ደብዳቤ ለአህዛብ አማኞች የተላከው በማን ሀላፊነት ነው?


© 2016 MentorLink International

# የትብብር እሴት ለውጥ . . . . . የቅርብ እይታ

**በትንንሽ ቡድናችሁ በዚህ የአመለካከት ለውጥ ዙሪያ ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች ተወያዩባቸው:**

1. ይህ የአመለካከት ለውጥ በአጠቃላይ ስለ ምንድነው? በራሳችሁ ቃል ግለጹ፡፡

2. ይህንን የአመለካከት ለውጥ በተመለከተ በሀገራችሁ ስላለው የመሪነት ባህል የግል ግምገማችሁ ምንድነው?

## የፍጹም ለውጥ እሴት #4 የግል ግምገማ

*ከዚህ በታች ባለው የፍጹም ለውጥ እሴት ባስተሳሰባችሁ ባመለካከታችሁ እንዲሁም በልምምዶቻችሁ የቱ ጋር እንዳላችሁ ገምግሙ፡፡ በመሀከለኛው ክፍል ላይ ካሉት ቁጥሮች እናንተ በተሰጡት መንታ ሀሳቦች አኳያ የቱ ጋር እንዳላችሁ በማክበብ አሳዩ፡፡ ለምሳሌ በስተግራ ባለው ሰንጠረዥ ውስጥ ያለው ሀሳብ ያብዛኛውን ጊዜ ማንነታችሁን የሚገልጽ ከሆነ ለራሳችሁ «1» ስጡ በቀኝ ያለው ከሆነ ደግሞ «10» ስጡ በመሀከል ካላችሁ «5» ስጡ በተጨማሪም ከበታች ላሉት እራስን የመመልከቻ ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡*

| አምባገነንነትና እኔ እበቃለሁ ባይነት | ... ወደ... | ትብብርና ህብረት |
|---|---|---|
| የቡድን ሥራ ብዙ ዋጋን የሚጠይቅ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። ለብቻችን ስንሰራ በውስጣችን አብረውን የተፈጠሩ ብቃቶች አሉ፡፡ | ***በጋራ መሥራት***<br>*1-2-3-4-**5**-6-7-8-9-10* | በህብረት መስራት እግዚአብሔርን ያስደስታል በተጨማሪም ቡድኑን ይባርካል፡፡ ለእኔ የቡድን ስራ የሚያስከፍለው ዋጋ ከውጤቱ አንጻር ተገቢ ነው፡፡ |
| ጥሩ መሪ ብቸኛ ነው መሆን ያለበት፡፡ ተጠያቂነቴ ለእግዚአብሔር ብቻ ነው በተጨማሪም ለደህንነት እርሱን ብቻ ነው የምታመነው፡፡ | ***ብቸኝነት***<br>*1-2-3-4-**5**-6-7-8-9-10* | እንደ መሪ ቡድንን ትልቅ ቦታ እሰጠዋለሁ፡፡ ይህም ለአገልግሎት ውጤታማነት ብቻ ሳይሆን ለራሴ ደህንነትና ዕድገት ስል እንጂ፡፡ |
| ድክመት አላሳይም ለትችትና እርማት በር አልከፍትም ምክንያቱም ይህንን ካላደረግሁ ሰዎች አይከተሉኝምና፡፡ | ***ድክመት***<br>*1-2-3-4-**5**-6-7-8-9-10* | አንድን ህብረተሰብ ስለሚገነባና ከእግዚአብሔር ዘንድ ሀይልን ስለሚያስለቅቅ እራስን በማዋረድ በግልጽነት ለመምራት እሞክራለሁ፡፡ |
| መሪ እንደመሆኔ መጠን ለሁሉም ነገረ መልስ እንዲኖረኝና አገልግሎት የማከናወን የሚያስፈልጉኝን ስጦታዎች ሁሉ እንዲኖሩኝ እሞክራለሁ | ***በሁሉም ብቁነት***<br>*1-2-3-4-**5**-6-7-8-9-10* | እንደ መሪ ለጥያቄዎች መልስን ለመፈለግ የሚረዳና ለውጤታማነት የሚያስፈልገውን ልዩ ልዩ ስጦታ ያላቸውን ሰዎች የያዘ ቡድን እፈልጋለሁ፡፡ |
| እንደ መሪ ለውጤታማነቴ ዋጋ ይገባኛል፡፡ ይህም ጥሩ ዝናንና ጥሩ የአገልግሎት መስመርን ይዘረጋል፡፡ | ***ዕውቅና***<br>*1-2-3-4-**5**-6-7-8-9-10* | እንደመሪ እግዚአብሔር ለፈቀደው ማንኛውም አይነት መልካም ዉጤት የቡድን አባላቶቼን ዕውቅና በመስጠት ለእግዙአብሔር ክብር እሰጣለሁ |
| እንደ መሪ የዛሬ ውጤት ለነገ የበለጠ የአገልግሎት እድል በርን እንደሚከፍት አውቃለሁ፡፡ | ***የአንድ ሰው ሥራ***<br>*1-2-3-4-**5**-6-7-8-9-10* | እግዚአብሔር ስራዬን እንደሰጠኝና ከእኔ የሚፈልገው መታመንን ብቻ እንደሆነ በማሰብ ስራዬን በእግዚአብሔር እጅ ላይ እጥላለሁ፡፡ |
| በቡድናችን ሁሉም ሰው እራሱን የመከለከያ ማስክ ያጠለቀ ነው የሚመስለው፡፡ ግልጽ ሆነን ለመቅረብ ደህንነት አይሰማንም፡፡ | ***አስተማማኝ ቦታ***<br>*1-2-3-4-**5**-6-7-8-9-10* | ቡድናችን እርስ በእርስ ድካማችንን የምንነጋገርበት የግንኙነት ነፃነት ያለበት ቦታ እየሆነ ነው። |
| ሁሉም ሰው በግሉ ቢሰራ ደስ ይለኛል፡፡ እያንዳንዳችን ክርስቲያናዊ ህብረቶችን የምናገኝባቸው ሌሎች ቦታዎች አሉን፡፡ | **የፈውስ ቤተሰብ**<br>*1-2-3-4-**5**-6-7-8-9-10* | ቡድናችን እንደ ቤተሰብ እየሆነ ነው ከልባችን በእግዚአብሔር ፊት ላለን እድገት እርስ በእርስ እንረዳዳለን፡፡ |
| በጋራ እንፀልያለን፡፡ ስንፀልይ ግን አድካሚ ስራና ውጤት አልባ እንደሆነ ሆኖ ነው የሚሰማን፡፡ የተሻለ እንዴት ማድረግ እንደሚቻል እኔ አላውቅም፡፡ | **በቡድን የሚደረግ ፀሎት**<br>*1-2-3-4-**5**-6-7-8-9-10* | ፀሎት ብዙ ነገሮችን ስለሚቀይር ቡድኑ ቅድሚያ የሚሰጠው ነገር አድርገነዋል፡፡ ጊዜውን በጠበቀ መልኩ በህብረትና አንዳችን ላንዳችን እንፀልያለን፡፡ |



© 2016 MentorLink International

## የእሴት ለውጥ #5: መሪዎችን አስቦ ማብዛት

### ከድንገተኛ መሪዎችን መጨመር ወደ ታሰበበት መሪዎችን ማብዛት

ኢንግዲህ ልጄ ሆይ አንተ በክርስቶስ ኢየሱስ ባለው ፀጋ በርታ፡፡ ብዙ ሰዎች የመሰከሩለትን ከእኔም የሰማኸውን ሌሎችን ደግሞ ሊያስተምሩ ለሚችሉ ለታመኑ ሰዎች አደራ ስጥ፡፡ ”
2ጢሞ 2፡1-2

በክርስቶስ ኢየሱስ እየተቀየረ ያለ መሪ. . . በአርአያነት ማስተማርን ቅድሚያ የሚሰጠው ነገር የሆነ፤ ተተኪ መሪዎችን ለማሳደግ ጊዜውንና ጥረቱን ያዋለ ነው፡፡.

### *እራስን መመልከት፡*

- የፍፁም ለውጥ እሴት የሆነውን የግል መንግስትን ከማሳደግ የእግዚአብሔር መንግስት ወደማሳደግ መምጣትን በተመለከተ በግል አመለካከታችሁ ልትለውጧቸው ስለሚገቡ ነገሮች እግዚአብሔር ምን እያላችሁ ነው?

- ከግራው ሰንጠረዥ ጋር ተጠብቃችሁ እንድትቀሩ ያደረጋችሁ ምንድን ነው? የምን ፍርሀት? ያለፍከው ልምምድ?

- በእናንተ እይታ በእውነት ከልቡ የተናዘዘ ሰው ምንን ይመስላል?

**በኢየሱስ አገልግሎት ውስጥ ያለ የግንኙነት ስልትና . . . የእኛ ስልት አጠቃላይ እይታ**




ከዚህ በላይ ካለው ስዕል ስለ ኢየሱስ ስልት ምን አዲስ እይታን ተማራችሁ?

የእናንተ የግንኙነት ስልት የኢየሱስን የግንኙነት ስልት በምን መልኩ ይመስላል? ስልታችሁ ከኢየሱስ ስልት እንዴት ነው የሚለየው?

በአገልግሎት ስልታችሁ ምን ዓይነት ለውጦችን ማምጣት ሊያስፈልጋችሁ ይችላል?


© 2016 MentorLink International

ኢየሱስ በዚህ ወቅት የእግዙአብሔር መንግስት ቀጣይነት እና የእኔና የእናንተን ቀጣይ ሕይወት ከፈተና ውስጥ ከቷል። ኢየሱስ ሆን ብሎ መሪዎች ላይ ያተኩር ነበር፡፡ መሪዎች ላይ የሚያተኩሩ . . . መሪዎች ላይ ማተኮሩ እጅጉን አስፈላጊ ነበር፡፡ ከዚህ በታች በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሌሎች የኢየሱስን ምሰሌነት የተከተሉ ቀርበዋል፡፡

- በርናባስ ጳውሎስና ዮሐንስን (ማርቆስ) ይዞ በአርአያ መሪነት ያስተምራቸው ነበር «በርናባስ ሳውልም አገልግሎታቸውን ፈጽመው ከኢየሩሳሌም ተመለሱ ማርቆስ የተባለው ዮሐንስንም ከእነርሱ ጋር ይዘውት መጡ» የሐ/ሥራ12፡25
- ጳውሎስ ጢሞቲዎስን ሉቃስን ጵርስቂላንና አቂላን እንዲሁም ሌሎችን በአርአያነት አስተምሯል «እንግዲህ ልጄ ሆይ አንተ በክርስቶስ ኢየሱስ ባለው ፀጋ በርታ፡፡ ብዙ ሰዎች የመሰከሩለትን ከእኔም የሰማህውን ሌሎችን ደግሞ ሊያስተምሩ ለሚችሉ ለታመኑ ሰዎች አደራ ስጥ፡፡» 2ጢሞ2፡1-2
- ጵርቂላና አቂላ አጵሎስን በአርአያነት አስተምረዋል ጵርስቅላና አቂላም በሰሙት ጊዜ ወስደው የእግዚአብሔርን መንገድ ከፊት ይልቅ በትክክል ገለጡለት፡፡ የሐ/ሥራ 18፡26

የሐዋ/ሥራ 19፡8-10ን በማጥናት ያልታሰበበት የመሪዎች መጨመር ከታሰሰበት መሪዎችን የማብዛት ሒደት ጋር ማነፃፀራችንን እንቀጥል፡፡ ይሄ በኤፌሶን የጢራኖስ አዳራሽ የተሰጠ ትምህርት ስለ ጳውሎስ በአርአያነት በማስተማር የማብዛት አገልግሎት የሚያወራ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ታሪክ ነው፡፡

- የሐ/ሥራ 19፡8-10 አንብቡ፡፡ ይህንን ታሪክ ስታነቡ ምን አስገረማችሁ ?
- እንደ ቤተክርስቲያን ተካይ በሐ/ሥ 13-18 ላይ ያለው የጳውሎስ ስልት ከዚህ ጋር በሐ/ሥራ 19፡8-10 ካለው በምን ይለያል? ጳውሎስ ከግራ በኩል የድምር መሪነት ወደ ግራ በኩል የማብዛት መሪነት እንዴት ነበር እየሄደ የነበረው?
- በቁጥር 10 መሰረት ጳውሎስ በኤፌሶን በነበረው አገልግሎት የተገኙ ውጤቶች ምን ምን ነበሩ? ይህ በራዕይ 2-3 ከሚገኙት 7 አብያተክርስቲያናት ጋር እንዴት ነው የሚዛመደው?
- ግልፅ የሆነ ምናባዊ ስዕልን በማሰብ በቁጥር 10 የተጻፈው ውጤት እንዲከሰት መንስኤ የሆነ በጤራኖስ አዳራሽ በየቀኑ ምን የተከሰተ ይመስላችኋል? ይህም በአሁኑ ጊዜ ሊኖራችሁ የሚገባ በአርአያነት የማብዛት አገልግሎት ምሳሌ ሊሆን የሚችለው እንዴት ነው?

በእነዚህ ጥያቄዎች ከፍለ ጊዜውን አጠናቁ

- ኢየሱስ ወይም ጳውሎስ ብዙ መሪዎችን በአንዴ ለማፍራት ሞክረው ያውቃሉ? ለምን?
- በአሁኑ ወንጌላውያን አብያተክርስትያናት የትኛው መሪ የበለጠ አትኩሮት ይሰጠዋል ? የሚጨምረው ወይንስ የሚያበዛው? አንድ ወይንም ሁለት ምሳሌ በመስጠት መልሳችሁን አብራሩ፡፡
- ከዚህ ቀጥሎ ካለው ሀሳብ ጋር በመስማማት ወይም ባለመስማማት መልሳችሁን ከሌሎች ጋር ተወያዩበት፡፡ አንድ መሪ አቅዶበት መሪዎችን እያሳደገ ካልሆነ እርሱ/እርሷ ኢየሱስንና ምሳሌውን እየተከተለ/እየተከተለች አይደሉም፡፡

## *የማብዛት እሴት ለውጥ . . . . . . የቅርብ እይታ*

**በትንሽ ቡድናችሁ በዚህ የአመለካከት ለውጥ ዙሪያ ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች ተወያዩባቸው፡፡**

1. ይህ የአመለካከት ለውጥ በአጠቃላይ ስለምንድነው? በራሳችሁ ቃል ግለጹ፡፡

2. ይህንን የአመለካከት ለውጥ በተመለከተ በሀገራችሁ ስላለው የመሪነት ባህል የግል ምልከታችሁ ምንድነው?


© 2016 MentorLink International

## የፍጹም ለውጥ እሴት #5 የግል ግምገማ

ከዚህ በታች ባለው የለውጥ እሴት ባስተሳሰባችሁ ባመለካከታችሁ እንዲሁም በልምምዶቻችሁ የቱ ጋር እንዳላችሁ ገምግሙ:: በመሐከለኛው ክፍል ላይ ካሉት ቁጥሮች እናንተ በተሰጡት መንታ ሀሳቦች አኳያ የቱ ጋር እንዳላችሁ በማክበብ አሳዩ:: ለምሳሌ በስተግራ ባለው ሰንጠረዥ ውስጥ ያለው ሀሳብ ያብዛኛውን ጊዜ ማንነታችሁን የሚገልጽ ከሆነ ለራሳችሁ «1» ስጡ በቀኝ ያለው ከሆነ ደግሞ «10» ስጡ በመሀከል ካላችሁ «5» ስጡ በተጨማሪም ከበታች ላሉት እራስን የማያ ጥያቄዎች መልስ ስጡ::

| መሪዎች በመጨመር ማደግ | … ወደ… | የታቀደ የመሪዎች ማብዛት |
|---|---|---|
| ብዙ ሰዎችን በስሬ ማድረግና ስለዚህም ማውራት ህልሜ ነው። የበላይ ተቆጣጣሪ መሆን እፈልጋለሁ፡ | የማብዛት ራዕይ<br>1-2-3-4-5-6-7-8-9-10 | የእኔ ራዕይ እንቅስቃሴን መምራት የሚችሉ፣ የሚያፈሩ መሪዎችን በማስታጠቅና በማብቃት ብዙዎች ወደደ ክርስቶስ ሲመጡ ማየት ነው:: |
| ለአንድ አገልግሎት በብዛትና በቁጥር ማደግ የውጤታማ አገልግሎት እጅግ አስፈላጊ ክፍል ነው:: | የቁጥር አስደሳችነት<br>1-2-3-4-5-6-7-8-9-10 | ጥቂት ሌሎች መሪዎችን በጥራት ማሳደግ ለረጅም ጊዜ ለሚደረገው የሙብዛት ሂደት ቁልፍ ነገር ነው:: |
| አዲስ እየወጡ ያሉ መሪዎችን ለማስተማር ችሎታው ፍላጎቱ እንዲሁም ጊዜው የለኝም:: በስራ የተጠመድኩ ነኝ:: | በአርአያነት የመምራት ቀዳሚነት<br>1-2-3-4-5-6-7-8-9-10 | አዳዲስ የሚነሱ መሪዎችን በአርአያነት መምራት ቀዳሚ ሥራዬ ነው ምንክያቱም ዘላቂነት ላለው ውጤታማነት ቁልፍ ነገር ነው:: |
| ስጦታዎቼን መጠቀም እጅግ ከመውደዴ የተነሳ አዲስ እየመጡ ላሉት መሪዎች አገልግሎቴን እንዲሁ በቀላሉ ልሰጥ አልችልም:: | የአገልግሎት ስኬት<br>1-2-3-4-5-6-7-8-9-10 | አዳዲስ ወጣት መሪዎች ሲያገለግሉ በማየት ለመደሰት የግሌ የሆኑ መሳካቶችን መስዋእት አደርጋለሁ:: |
| አብዛኛውን ጊዜ አገልግሎታችንን እንዲመሩ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች ወይም በሌሎች የሰለጠኑ ሰዎችን እንጠቀማለን:: | የመሪነት እድገት<br>1-2-3-4-5-6-7-8-9-10 | የራሳችንን መሪዎች በመላው ሰው ልብ ችሎታና ዕውቀታቸው ላይ በማተኮር እናሰለጥናለን። |
| መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውቀትንና የመሪነትን ችሎታ ለመስጠት ስልጠናን እንጠቀማለን። | የባህርይ ሽግግር<br>1-2-3-4-5-6-7-8-9-10 | አምላካዊ ባህሪዎችህን ለመቅረጽ ቁልፍ ስለሆነ ሰዎችን በአርአያነት እናስተምራለን:: ይሄ ለአመራርና ለሙብዛት ውጤታማነት ማዕከላዊ ነው። |
| ብዙ መሪዎች ያስፈልጉናል ነገር ግን በአገልግሎቴ የተጠመድኩ ስለሆንኩ ይህን ለማድረግ በቂ ጊዜ የለኝም | እቅዳዊነት<br>1-2-3-4-5-6-7-8-9-10 | በጥቂት አዳዲስ መሪዎች ላይ ሆን ብዬ ህይወቴን አፈስሳለሁ። |
| በፀሎት አምናለሁ ነገር ግን እየሰራሁ ላለሁት ስራ ማዕከላዊ ነገር ለማድረግ ጊዜውና ትኩረቱ የለኝም:: | ለሙብዛት መፀለይ<br>1-2-3-4-5-6-7-8-9-10 | ታላላቅ የእግዚአብሔር ሥራ እንቅስቃሴዎች ሁልጊዜም በፀሎት ላይ የተመሰረቱ ናቸው:: ስለዚህ ጸሎት የእንቅስቃሴያችን እና የማንነታችን ዋና አካል ነው:: |

## እራስን መመልከት፡-

- የፍፁም ለውጥ እሴት የሆነውን የግል መንግስትን ከማሳደግ የእግዚብሔር መንግስት ወደማሳደግ መምጣትን በተመለከተ በግል አመለካከታችሁ ልትለውጧቸው ስለሚገቡ ነገሮች እግዚአብሔር ምን እያላችሁ ነው?
- ከግራው ሰንጠረዥ ጋር ተጠብቃችሁ እንድትቀሩ ያደረጋችሁ ምንድነው? የምን ፍርሀት? ምን ያለፉ ልምምድ?
- በእናንተ እይታ በእውነት ከልቡ የተናዘዘ ሰው ምንን ይመስላል?


© 2016 MentorLink International

# ክፍል 3 – ክርስቶስን ማዕከል ያደረጉ መሪዎችን በማሳደግ ውስጥ የሚያስፈልጉ ችሎታዎች

## ታሪካችሁን መናገር

### በትረካ ውስጥ ያለ ሃይል

- በአለም ላይ በሁሉም ባህል ትረካ ታሪኮችን ለመናገርና የእሴት ለውጥ ለማምጣት ለረዥም ጊዜ ዋነኛ መንገድ ሆኖ ቆይቷል፡፡
- ታሪኮች ልብን ስሜትን አስተሳሰብንና አእምሮን ይይዛሉ፡፡
- እግዚአብሔር በሕይወታችሁ እንዴት እየሰራ እንዳለ የሚያሳየው የእናንተ ምስክርነት (ታሪክ) የወንጌልን ሀያልነት አሳማኝና አመላካች አዋጅ ነው፡፡

### መጽሐፍ ቅዱሳዊ የትረካ ምሳሌዎች

- በፊሊጵ 3፡2-4 የሚገኘውን የጳውሎስ ታሪክ አንብቡ። ጳውሎስ የግል ህይወቱን ወይንም ታሪኩን የማሳየቱ አላማ ለምን እንደሆነ የግል አመለካከታችሁን በፅሁፍ አስፍሩ።

### እንደ ምሳሌ አንድ ሰው ታሪኩን ይናገር

### አጋጣሚውን ታሪካችሁን ለማዘጋጀትና ለመናገር ተጠቀሙበት። የሚከተሉትን ነጥቦች ከግምት ውስጥ አስገቡ

- ✓ የመጣችሁበትን ቤተሰብ ታሪክ
- ✓ የልባችሁን መሰበር:
    1. በጉድለታችሁ አስተዋፅኦ ያደረጋችሁበት መንገድ
    2. በህይወታችሁ የልብ መሰበር ያደረሱባችሁን ልትቆጣጠሯቸው ያልቻላችኋቸው አጋጣሚዎች
- ✓ እግዚአብሔር በህይወታችሁ መፅናናትን እንዴት እንዳመጣ
- ✓ እግዚአብሔር  እንዴት ከግራ ወደ ቀኝ እንዴት እያሸጋገራችሁ እንዳለ


© 2016  MentorLink International

# በአርአያነት የመምራት ችሎታዎች:

## በአርአያነት የመምራት ግንኙነት የመመስረቻ ደረጃዎች

ለመጀመር ከዚህ በታች የተሰጡትን ደረጃዎች አንብቡ። በቀኝ በኩል በሚገኘው ክፍት ቦታ ላይ ምልከታችሁን ፃፉ።

1. **መፀለይ** ሌሎችን በአርአያነት ለመምራት የሚያስከፍለውን ዋጋ ማወቅ። በአርአያነት የሚመራው ቡድን ውስጥ ማን ማን እንደሚካተት ለመምረጥ እግዚአብሔር ጥበብን እንዲሰጣችሁ መጠየቅ። (ሉቃስ 6:12-13)

2. የምትፈልጉትንና የሚያስፈልጋችሁን አይነት በአርአያነት የመምራት ግንኙነት **መወሰን**: ታናሽ፣ እኩያ ወይም ታላላቅ መሪዎች

3. ከአንድ እስከ አምስት አባል ያለበት **በአርአያነት የሚመራ ቡድን መምረጥና መመስረት።** ታማኝ የሆኑትን ፈልግ (2 ጢሞ 2:2; ሉቃስ 6:14-15)። እነዚህን ሰዎች ተፅዕኖ ማድረግ ከምትችሉት የቤተብ አባል፣ ጓደኛ፣ የስራ ባልደረባ ወይም የጋራ ፍላጎት ካላቸው ሰዎች መምረጥ ትችላላችሁ።

4. የቡድን **ግንኙነት በመገንባት** ጊዜ **ወጥ የሆነ የግንኙነት ጊዜ** አሳልፉ  (1 ተሰሎንቄ 2:7-12)

   - በቀላሉ በቤት ውስጥ፣ በስራ ቦታ፣ ወዘተ አብራችሁ ሁኑ
   - ወጥ የሆነ የመገናኛ ጊዜ አብራችሁ ወስኑ
   - እርስ በእርስ አዝናኝ የሆኑ ነገሮችን አድርጉ
   - በአገልግሎት ጊዜ አብራችሁ ሁኑ
   - እርስ በእርስ ታሪካችሁን ተነጋገሩ፣ እንዲሁም ግልፅነትን ተለማመዱ

5. **እርስ በእርስ የእያንዳንዳችሁን ልብ ተዋወቁ፣** በደንብ በመስማትና የሚቀሰቅሱ ጥያቄዎችን በመጠየቅ  (ያዕቆብ1:21)

6. **መፅሀፍ ቅዱስን በጋራ ማጥናት፤** ቁልፍ በሆኑ የህይወታችሁ ጎኖች የእግዚአብሔርን መልስ መፈለግ። በተጨማሪም **አንድ መፅሀፍ ምረጡና አንብባችሁ**  ተነጋገሩ፣ ተበረታቱ

7. በእያንዳንዳችሁ ህይወት ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔርን **ጥሪና ስጦታዎች**  መለየትና ማሳደግ

8. **ደካማ ጎናችሁን ማየትና በዛ አቅጣጫ ማደግ።** ይህ ማለት ጥሪያችሁን ለመፈፀም እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ ጉዳዮችን ማለት ነው።  ደግሞም እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችሁ ለገለጠው

   ነገር እርስ በእርስ ተጠያቂ ሁኑ።

9. **ሌሎች በአርአያነት የሚመሩ ቡድኖችን** ለመመስረት ዕቅድ ይኑራችሁ።

10. ተጨማሪ ሀሳብ አላችሁ?



© 2016  MentorLink International

# ክፍል 4 -ክርስቶስን ማዕከል ያደረጉ መሪዎችን በማሳደግ እንቅስቃሴ ውስጥ ከእግዚአብሔር ጋር መተባበር

በሕይወታችሁና እግዚአብሐር እንድትሳተፉበት ባደረጋችሁ አገልግሎቶች ውስጥ ሁሉንም መስመሮች በአንድነት የማምጫ ጊዜው አሁን ነው፡፡

"ማስተላለፍ!" የሚለው የዚህ ስልጠናችን የመጨረሻ ግብ ፤ አሁን ካላችሁበት መሆን ወደምትፈልጉበት የሚወስዳችሁ ተግባር ዕቅድ እንዲኖራችሁ ማድረግ ነው። ነገር ግን ይህንን ከማድረጋችን በፊት መጽሐፍ ቅዱስ ስለ አርአያዊ መሪነት እንቅስቃሴዎች ምን እንደሚልና ይህም እኛንና የምንመራቸውን እንዴት ሊጠቅም እንደሚችል እንመልከት

በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን ውስጥ ያሉ አንዳንድ የእንቅስቃሴ ምሳሌዎች

**ልዩ ክፍል፡**

**በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉት የእግዚአብሔር እንቅስቃሴዎችና በአሁኑ ጊዜ ያሉት እንቅስቃሴዎች**

| የብሉይ ኪዳን እንቅስቃሴዎች | የአዲስ ኪዳን እንቅስቃሴዎች |
| --- | --- |
| • ኢያሱ<br>• ዳዊት<br>• አሳ (ህዝቂያስ)<br>• እዝራ (ነህምያ)<br>• አስቴር/መርዶኪዮስ<br>• ዳንኤልና ጓደኞቹ | • መጥምቁ ዮሐንስ/ኢየሱስ<br>• ሰማርያ (ዮሐንስ 4 እና የሐ/ሥራ 8)<br>• ኢየሩሳሌም (የሐ/ሥራ 2)<br>• የጳውሎስ ቤተክርስቲያን የመትከል አገልግሎት<br>• ኤፌሶን (የሐ/ሥራ 19፡8-10)<br>• ተሰሎንቄ (1 ተሰሎንቄ 1፡7-8) |

## የአፈሮቹ/ የዘሪው ምሳሌ እና እንቅስቃሴዎች፡ ማቴ 13፡18-23

ይህ ምሳሌ አብዛኛውን ጊዜ ከወንጌል ስርጭት አንፃ ነው የሚታሰበው። ነገር ግን ኢየሱስ እዚህ ጋር የተናገረውን እኛ ስለ እንቅስቃሴዎች እንዲናገረን እንፍቀድለት፡-

"እንግዲህ እናንተ የዘሪውን ምሳሌ ስሙ። የመንግስትን ቃል ሰምቶ በማያስተውል ሁሉ ክፉው ይመጣል በልቡ የተዘራውንም ይነጥቃል በመንገድ ዳር የተዘራው ይህ ነው፡፡ በጭንጫ ላይ የተዘራውም ይህ ቃሉን ሰምቶ ወዲያው በደስታ የሚቀበለው ነው፤ ነገር ግን ለጊዜው ነው እንጂ በእርሱ ስር የለውም በቃሉ ምክንያትም መከራ ወይንም ስደት በሆነ ጊዜ ወዲያው ይሰናከላል። በእሾህ መካከል የተዘራውም ይህ ቃሉን የሚሰማ ነው የዚህም አለም ሀሳብና የባለጠግነት መታለል ቃሉን ያንቃል የማያፈራም ይሆናል። በመልካም መሬት የተዘራውም ይህ ቃሉን ሰምቶ የሚያስተውል ነው እርሱም ፍሬ ያፈራል አንዱም መቶ አንዱም ስድሳ አንዱም ሰላሳ ያደርጋል፡፡


© 2016 MentorLink International

- በመጀመሪያዎቹ ሶስቱ አፈሮች ላይ የነበረው ችግር ምን ነበር? ይህ እንቅስቃሴዎች እንዳይጀመሩ ወይም እንዳያድጉ እንቅፋት ከሚሆኑ ነገሮች ጋር የሚያገናኘው ምንድነው?
- አራተኛው የአፈር አይነት እንቅስቃሴን እንዴት ነው የሚወክለው?
- ኢየሱስ ስለተለያዩ ውጤቶች የተናገረው ለምን ይመስላችኋል?
- በዚህ ምሳሌ ላይ በመመርኮዝ ስለ እንቅስቃሴ ምን ተጨማሪ አመለካከት አላችሁ?

## በተቋሞችና በእንቅስቃሴዎች መሀከል ያሉ ልዩነቶች

በትንንሽ ቡድኖች ሆናችሁ በተቋሞችና በእንቅስቃሴዎች መሀከል ያሉትን ልዩነት መዝግቡ እንዲሁም ግምገማችሁን ሁሉም እንዲያዩት አድርጋችሁ መዝግቡ። ለማስጀመር ያክል አንዳንድ ሀሳቦች ከዚህ በታች ባሉት ሁለቱ ሳጥኖች ውስጥ ቀርበዋል፡፡

| ተቋሞች | እንቅስቃሴዎች |
| --- | --- |
| 1. ፕሮግራሞች | 1. ግንኙነቶች |
| 2. ብዛት እጅጉን አስፈላጊ ነው | 2. ጥራት እጅጉን አስፈላጊ ነው |
| 3. ከላይ ወደታች የሆነ የአመራር ስርአት | 3. ከታች ወደ ላይ (መሰረታዊ) የአመራር ስርአት |
| 4. ድርጅታዊ | 4. ህይወት ያለው አንድ አካል |
| 5. ሌሎች ሀሳቦቻችሁን ከዚህ በታች ጻፉ | 5. ሌሎች ሀሳቦቻችሁን ከዚህ በታች ጻፉ |

## የመጨረሻ አንዳንድ እራስን መገምገሚያ መጽሐፍ ቅዱስዊ እንቅስቃሴዎች . . .

- <u>እግዚአብሔርን በፀሎት በመጠበቅ ውስጥ መጽናት</u>

1. የሐ/ሥራ 1፡4 ወደ የሐ/ሥራ 2፡1-47 ይመራል (የክርስቶስ ተከታዮችን ቁጥር ማብዛት)
2. የሐ/ሥራ 12፡5 ወደ የሐ/ሥራ 12፡6-17 ይመራል (እየተሰቃዩ ያሉትን የእግዚአብሐር አገልጋዮችን በመለኮታዊ ሀይል ማውጣት)
3. የሐ/ሥራ 13፡1-3 ወደ የሐ/ሥራ 13፡4-14፡28 ይመራል (ቤተክርስቲያናትን ማብዛት)

- <u>በሁለት ቁልፍ በሆኑ የመሪዎች አይነት መመራት፣ አሸናፊዎችና ጣልቃገቦች</u>

1. አስቴር (የምትታይ አሸናፊ) እና መርዶኪዮስ (የማይታይ ጣልቃገብ)
2. ነህምያ (የሚታይ አሸናፊእ) እና ዕዝራ (የማይታይ ጣልቃገብ)
3. ኢየሱስ (የሚታይ አሸናፊ) እና መጥምቁ ዮሐንስ (የማይታይ ጣልቃገብ)
4. ጳውሎስ (የሚታይ አሸናፊ) እና በርናባስ (የማይታይ ጣልቃገብ)

- <u>አብዛኛውን ጊዜ ከሁለት ትውልድ በላይ አይቀጥልም</u>

1. ሙሴና ኢያሱ፤ ከዚያ መሳፍንት 2:10
2. ዳዊትና ሰለሞን፤ ከዚያ 1ነገስት 11
3. የሐዋርያት ስራ 19፡8-10 (ቀዳማይቱ የኤፌሶን ቤተክርስቲያን) እና ራዕይ 2፡1-7 (የሁለተኛው ትውልድ የኤፌሶን ቤተክርቲያን)


© 2016 MentorLink International

**በመጨረሻም በትንንሽ ቡድኖቻችሁ፣ በሀገራችሁ ወይንም በአገልግሎት ቦታችሁ እንቅስቃሴ ምን ሊመስል እንደሚችል በመግለጽ መዝግቡ፡፡**

**ልዩ ክፍል፡**

ከድርጅት ባህል ጋር የሚገናኙ ጉዳዮች እና ፈተናዎች

ይህ የመጨረሻው ትምህርት ክርስቶስን ማእከል ያደረግ፥ ክርስቶስን የሚመስል ህይወት ለመምራት የወሰኑ መሪዎችን በብዛት የሚያደናቅፉ ዋና ጉዳዮችን ለመድረስ ይሞክራል። ይህ በጣም አስፈላጊ ለሆነ ርዕስ እንደመግቢያ የሚሆን ነው። የበለጠ ትኩረት፥ውይይት እና ፀሎት የሚስብ ነው።

እስካሁን ድረስ በስልጠናችን መሪዎች ከግራ ወደ ቀኝ ለመሄድ እንዴት እና ለምን እየሱስ መከተል እንዳለባቸው፥ በባህሪው እና በአገልግሎት ዘይቤው እንዴት ሊመስሉት እንደሚገባ ትኩረት ሰጥተን ቆይተናል።

ይሁን እንጂ ብዙ መሪዎች ክርስቶስን እና በአርአያነት የማስተማር ዘዴውን መከተል የተወሳሰበ እና ከባድ እንደሆነ ሀሳባቸውን ሰጥተዋል። ይህንን ሊሉ የቻሉበት ምክንያት የሚያገለግሉበት ቤተክርስቲያናቸው እና ክርስቲያናዊ ድርጅቶች የአገልግሎት መዋቅር፥በእሴት፥በራዕይ እና በአፍፃፀም ግራ ዘመም መሆናቸው ነው።

ለእንደዚህ አይነት ተግዳሮት መሰረት የሚሆኑ ቢያንስ ሶስት የተለመዱ ችግሮች ይኖራሉ፡

1. በመጀመሪያ፥ አገልግሎትን የሚመሩ አካላት በሚጠብቁት ነገር እና በእይታቸው አብዛኛውን ጊዜ ስጋዊ ይሆናሉ። በቁጥር የሚለካ ውጤት ማግኘት ቅድሚያ የሚሰጡት ነገር ሲሆን ወይም ከሆነ (ለምሳሌ፥ የገንዘብ ስጦታን ለመጨመር ወይም የተሳታፊዎችን ቁጥር ለመጨመር ፥ ብዙ የተለወጡ ሰዎችን መፈለግ፥ ወዘተ) ። ውጤቱ ፈታኝ ፥ግራ ዘመም የሆነ የአገልግሎት ሁኔታን መፍጠር ነው።
2. በተጨማሪ ቤተክርስቲያናት እና ክርስቲያናዊ ድርጅቶች በብዛት ግራ ዘመም በሆኑ ሽማግሌዎች ይመራሉ። በዚህ ሁኔታ ለውጥ ለማምጣት ስልጣን ያላቸው እነዚህ ሰዎች ብቻ ናቸው። ስለዚህ ታዳጊ መሪዎች ወደ ቀኝ ጎን ሲያመዝኑ እነዚህ ሽማግሌዎች ፍራቻ ያድርባቸዋል። ጉዳዩ ከእጃቸው ከመውጣቱ በፊት የበለጠ ግራ ዘመም የሆነ አመለካከት በመያዝ በአጀንዳ እና በሰዎች ላይ ያላቸውን ስልጣን ለመጠበቅ ይነሳሳሉ።
3. በመጨረሻም፡ አብዛኞቹ ክርስቲያናዊ አገልግሎቶች ብዙ ጊዜ በይፋ ከመፅሐፍ ቅዱስ የሚያጣቅሷቸው እሴቶች በይፋ የሚለማመዷቸው አይደሉም። ስለ አገልግሎቱ በግልፅ የተቀመጡ እሴቶች ቢኖሩ እንኳን እውነተኞቹ ወይም የሚተገበሩት እሴቶች የሚገለጡት መሪዎች ቁልፍ ለሆኑ ጉዳዮች በሚኖራቸው ምላሽ ይገለጣል።

አርአያ በሚሆነው ቡድን ውስጥ በመሆን የሚከተለውን ታሪክ አብራችሁ አንብቡ

አንዲት ታዋቂ በሆነች ቤተክርስቲያስን አንድ ወጣት የሆነ መሪ በወጣቶች መሀል መልካም የሆነ አገልግሎት ነበረው። ይህ መሪ ከቀደሙት ታላላቅ መጋቢዎች የተለየ አመልካከት ያሳይ ስለነበር በተደጋጋሚ በይፋ ይወገዝ ነበር። እንደ ስራ ባልደረባ አንድ የሚናገረው ነገር እንዲሁም ልምድ እንዳለው ሰው ተቀባይነት እንደሚኖረው ያስባል።ያሉትን ሀሳቦች ጫና ሰጥቶ ለመግለፅ አይሞክርም። ይሁንእንጂ የሚናገራቸው አመለካከቶቹ ሀላፊነት ላለመውሰድ እንደሚደረጉ ተደርገው ይወሰዳሉ። ይህ ከቀደሙት ቤተክርስቲያኖች አንዱ በመሆኑ፥ መጪው ጊዜ ላይ ያተኮረ እና አዳዲስ ሀሳቦች የሚያብቡበት ይሆናል የሚል ሀሳብ ነበረው። በዚህ ፋንታ ከፍተኛ መጋቢው ስነ ስርአት ሊያስይዘው ይሞክራል። ከዚህ በተጨማሪ ወጣት መሪዎችን ያጣጥላል። ወጣት መሪዎች ነገሮችን በሌላ መልኩ እንዲመለከቱ ከማበረታታት ይልቅ በየጊዜው እያጣጣለ ይናገራቸዋል። ሁኔታው ከመጥፎ ወደ ከፋ ደረጃ ደረሰ። አንድ የቤተክርስቲያን ሽማግሌ እያንዳንዱን እንቅስቃሴውን እንዲከታተል ከተመደበ በኋላ ወጣቱ መሪ በእያንዳንዱ ነገር ቁጥጥራቸው ውስጥ ነበር። አዋቂነቱን እና ለራሱ ያለውን ዋጋ


© 2016  MentorLink International

አሳጡት። በመጨረሻም ከቤተክርስቲያን ለቀቀ፥ተዋረደ፥ተሰበረ። (በኮሊን በክላንድ እና ሪክ ሴሶ ክራፍቲን ኤ ካልቸር ከተሰኘው መፅሐፍ ላይ የተወሰደ። ገፅ:11)

## ለቡድናችሁ የሚሆን የመወያያ ጥያቄ

1. ይህ ታሪክ እስከ አሁን ድረስ ስንመለከተው ከቆየነው ሀሳብ ጋር በምን ይገናኛል።
2. ይህ መጥፎ አጋጣሚ እንዲፈጠር አስተዋፆ ያደረጉ ከከፍተኛ መሪዎች ጋር የተገናኙ እንዲሁም ድርጅታዊ የሆኑ ጉዳዮች ምንድን ናቸው።
3. ከዚህ በፊት በአገልግሎት ላይ የገጥሙህ ወይም አሁን እየገጠሙህ ያሉ ተሞክሮዎች ከዚህ ታሪክ ጋር ተመሳሳይነት አላቸው? ከዚህ የተነሳ የገጠመህ ነገር ምንድን ነው? በቤተክርስቲያንህ ወይም በድርጅቱ ውስጥ ምን ተፈጠረ።

## ድርጅታዊ ውድቀትን መረዳት

ጂም ኮሊንስ ውጤታማ የሆኑ ድርጅቶች በጣም ገነው ቀስ በቀስ እየወረዱ ሄደው በመጨረሻም ስለሚወድቁበትን ምክንያት ጥልቅ የሆነ ጥናት ያደረገ በጣም ምርጥ ፀሀፊ ነው። ግዙፉ እንዴት እንደሚወድቅ (ሀው ዘ ማይቲ ፎል) በተሰኘው መፅሐፉ የሰጠውን ማጠቃለያ ስንመለከት ሁሉም ውጤታማ የሆኑ ክርስቲያናዊ ድርጅቶች ለውድቀት የሚዳረጉበት የጋራ የሆነ ምክንያትን ያሳያል። ግራ ዘመም የሆነ አመራር ዘዴ ያላቸው አገልግሎቶችም ከዚህ አያመልጡም።

የኮሊን ጥናት የውድቀትን አምስት ደረጃዎችን አስቀምጧል።እነዚህ ደረጃዎች እያደጉ የሚሄዱ በሽታዎች ናቸው። በእንጭጭ እድሜው ላይ እያለ በሽታውን ማወቅ በአጠቃላይ ከባድ ነው፥ነገር ግን በዛ ደረጃ ላይ ሳለ ነው ማዳን የሚቻለው። ከዘገየ በኋላ በሽታውን ማግኘት ቀላል ይሆናል ነገር ግን ለውጥ ለማምጣት ከባድ ይሆናል። የሱ ሀሳቦች ድርጅቶችን ያማከሉ በሚሆንባቸው ቦታዎች በሙሉ ክርስቲያናዊ አገልግሎት የሚለውን ቃል እንጠቀማለን ይህም እነዚህ ደረጃዎች ለሁለቱም አንድ እንደሆኑ ስላጠቃለልን ነው።

አምስቱ የውድቀት ደረጃዎች እንደሚከተለው ተለይቶ ቀርቧል።





© 2016  MentorLink International

**ደረጃ 1፡ ከቀደመው ስኬት የሚወለድ ኩራት**

ክርስቲያናዊ አገልግሎቶች ፥ ልክ እንደሰው ስኬታማ ሲሆኑ እብሪተኞች ይሆናሉ። ራስን ዝቅ ማድረግ እና ልቆ በመገኘት ላይ ትኩረት ማድረግ የውጤታማነት መሰረታዊ ቁልፎች ናቸው። ከሁሉ የበላይ ስትሆን ማን እና እንዴት እዛ እንደደረስክ ማገናዘብ ታቆማለህ። ይገባኛል የሚል ስሜት ይታያል።

**ደረጃ 2፡ ያልተገራ ፍላጎት**

ክርስቲያናዊ አገልግሎቶች እድገት ላይ በጣም ሲያተኩሩ እዛ ቦታ ምን እንዳደረሳቸው ይረሳሉ፥ለዋናው ጥማታቸው ያላቸው ያልተከፋፈለ ትኩረት፥ተሰጥኦ እና እምቅ ሀብታቸው።ግራ ዘመም አገልግሎቶች እና መሪዎች ውጤታማነት እንዲሁም ለራሳቸው እና ለስራቸው ስም ማስቀረት ላይ ትኩረት ያደርጋሉ።

**ደረጃ 3፡ ያለውን አደጋ መካድ እና ማሽቆልቆል**

አገልግሎቶች ትኩረት እንዲሰጡት የሚነገራቸውን ነገር እውነታውን መጋፈጥ አይፈልጉም። አስጊ የሆኑ ምልክቶች ሲገለጡ እንኳን አዎንታዊ የሆነውን በማጉላት አሉታዊ የሆኑትን እንቀንሳቸዋለን።

**ደረጃ 4፡ መዳንን አጥብቆ መፈለግ**

ድርጅታዊ ማሽቆልቆል ግልፅ ሲሆን አገልግሎቶች ፈጣን የሆነውን መፍትሄ ይወስዳሉ( ለምሳሌ ፥አዲስ ሽማግሌ መምረጥ፥የአላማ/የራዕይ መግለጫ ቃላትን መቀየር፥ራስን ማስተዋወቂያ መንገዶችን መቀየር፥አዳዲስ ሊጋሾችን ማግኛ መንገዶችን መቀየስ፥የመሳሰሉት) አንድን ነገር በትክክል ያለመስራት አሻራ ለለውጥ ፍላጎት አለማሳየት አይደለም ነገር ግን አደገኛ በሆነ መልኩ አንድአይነት አለመሆን ነው።

**ደረጃ 5 ሊወገድ ለማይችለው ድርጅታዊ ሞት እጅ መስጠት**

እዚህ ደረጃ ላይ የደረሱ ክርስቲያናዊ አገልግሎቶች አብዛኛውን ጊዜ ተስፋ የቆረጡ እንዲሁም ምንም መፍትሄ ያጡ ናቸው። በዚህ ጊዜ የደረሰው ጉዳት በማይጠገንበት ደረጃ ደርሷል ማለት ነው።

## የውይይት ጥያቄዎች

1. ስለ ኮሊን ጥናት እና ማጠቃለያ ያላችሁ አመለካከት ምንድን ነው ?
2. በእነዚህ የድርጅታዊ ውድቀት ደረጃዎች ውስጥ እያለፈ ያለ አገልግሎት ውስጥ አባል ሆነህ ታውቃለህ? የችግሩ አካል ነበርክ? ወይስ የሚሰምጠውን መርከብ ለማዳን ከሚሞክሩት መሀል ነበርክ።
3. ወደ እዛ ቦታ መመለስ ብትችል የትኛውን ነገር በተለየ መልኩ ታደርገዋለህ?

## ለድርጅታዊ ለውጥ ወደ መፍትሄው መሄድ

ኮሊን በክላንድ እና ሪክ ሴሶምስ ክራፍቲንግ ኤ ካልቸር (ባህልን መቅረፅ)፡ የመሪ እጀታ ለድርጅታዊ ጤንነት በሚል ርዕስ በፃፉት መፅሐፍ፥ ጠቃሚ የሆኑ ሀሳቦችን ጠቁመዋል (የሚከተለው ገፅ 20፥21 ላይ ያለው ማሻሻያ ነው። )

ድርጅቶች እና መሪዎች እንዴት ነው የሚቀየሩት? ጤናማ ሆነው መጀመር ወይም ወደ ጤናማነት መመለስ የሚችሉት እንዴት ነው? በመጀመሪያ እግዚአብሔር ህይወታችንን የሚለካው ከሁሉ አስቀድሞ በምናፈራው ፍሬ ወይም በቁጥር በሚለካ ውጤት ሳይሆን በታማኝነታችን እንደሆን እውቅና ልንሰጠው ይገባል። ቁጥሩን ለመጨመር እርሱ ብቻ ነው ሀላፊነት ያለበት፥ እኛ ሀላፊነታችን ዘሩን መትከል እና ማጠጣት ነው (1ኛ ቆሮንቶስ 3፡6፤7። ሁለተኛ መለወጥ እንደምንችል ልናውቅ ይገባል። እንዲሁም ድርጅታችን መቀየር እንደሚችል። ይህ ነው የወንጌል ፍይዳ።


© 2016 MentorLink International

ይህን እውነታ ይዘን፥ አምስት ጥያቄዎችን በመጠቀም ድርጅታችን አሁን ያለውን ባህል ማጥናት መጀመር እንችላለን ። እነዚህ ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው።

1. የድርጅቱ መሪዎች ትኩረት የሚሰጡት እና የሚመዝኑት ነገር ምንድን ነው?
2. የድርጅቱ መሪዎች ወሳኝ ለሆኑ ገጠመኞች እና ድርጅታዊ ቀውሶች ምላሽ የሚሰጡት እንዴት ነው?
3. የድርጅቱ መሪዎች ያላቸውን ሀብት እንዴት ነው የሚጠቀሙት?
4. የድርጅቱ መሪዎች ምሳሌ የሚያደርጉት እና የሚያስተምሩት ነገር ምንድን ነው?
5. የድርጅቱ መሪዎች ሽልማቶችን እና ማዕረግን የሚሰጡት እንዴት ነው?

እነዚህ ጥያቄዎች በመጠቀም መሪዎች የድርጅታቸውን ባህል እንዲሁም የተጠቀሰው ባህል ከእውነተኛው ባህል እንዴት እንደሚለይ ሊመዝኑበት ይችላሉ ። የነዚህ ጥያቄዎች ምላሽ መሪዎች ድርጅታቸውን ወደ ጤናማ ለውጥ ለመምራት ከስር መሰረቱ በድጋሚ ውጤታማ በሆነ መልኩ የመጀመር አሉታዊ ጎኖችን የሚያዩበት ችሎታ ይሰጣቸዋል።

## ማጠቃለያ

በትንሽ ቡድን ሆናችሁ ከጥያቄዎቹ መሀል አንዱን ወይም ሁለቱን በመምረጥ የምታገለግሉበት ክርስቲያናዊ አገልግሎት መዝኑ። የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከመለሳችሁ በኋላ በፀሎት ጨርሱ።

1. ስለ አገልግሎታችሁ ድርጅታዊ ባህል ያለው መልካም ዜና ምንድን ነው?
2. ስለ አገልግሎታችሁ ድርጅታዊ ባህል ያለው መልካም ያልሆነ ዜና ምንድን ነው?
3. በአገልግሎታችሁ ባህል ውስጥ አዎንታዊ ለውጥ ለማምጣት እንደመጀመሪያ የሚሆኑ እግዚአብሔር እንድትተገብሩት የሚመራችሁን ሀሳቦች ዘርዝሩ።
    1.
    2.
    3.
4. በፀሎት ዝጉ

## የተግባር ዕቅድ

በዚህ ሳምንት እግዚአብሔር ለሕይወታችሁ የተናገራችሁ እጅግ በጣም አስፈላጊ የሆኑ የግል መልዕክቶች ምን ምን ነበሩ?

1.
2.
3.

እግዚአብሔር በግል እንድትሰሩት የነገራችሁን ነገሮች ተግባር ላይ እንዳታውሉ በመሰረታዊነት እንቅፋት የሆኑ ነገሮች ምን ምን ናቸው?

1.
2.
3.


© 2016 MentorLink International

ከሰማያዊ መምህራችሁ መንፈስ ቅዱስ ጋር በሚኖራችሁ ትብብር በአርአያነት የመምራት የኑሮ ዘይቤን እንድትጀምሩ ወይንም እንድታሳድጉ ምን ምን ነገሮች አፋጣኝ ትኩረት ያሻቸዋል?

1.
2.
3.

የአርአያነት ግንኙነቶቻችሁ ሊሆኑ የሚችሉ ግንኙነቶ የትኞቹ ናቸው? (የቤተሰብ አባላትን በመጨመር)

- ተመሳሳይ አርአያዊ ቡድን፡
  ____________________________________________________
  ____________________________________________________
- "ጢሞቴዎሶች"
  ____________________________________________________
  ____________________________________________________
- "ባርናባሶች"
  ____________________________________________________
  ____________________________________________________
- "ጳውሎሶች"
  ____________________________________________________
  ____________________________________________________

በአርአያነት መምራትን ለመጀመር፥ በአርአያነት በመምራት ለማደግ ወይንም አርአያ በሚሆኑ ሰዎች ለመመራት ልታደርጓቸው የምትችሏቸውን የተለያዩ ነገሮች ጥቀሱ፡፡

1.
2.
3.


© 2016  MentorLink International

አሁን በአገልግሎታችሁ ወይንም በድርጅታዊ ቡድናችሁ ውስጥ ከሚገኙ ሌሎች ሰዎች ጋር ተሰብሰቡ፡፡ በደንብ በማገናዘብ ከዚህ በታች ላሉት ጥያቄዎች የምትሰጡትን ምላሽ መዝግቡ፡፡

በዚህ ሳምንት እግዚአብሔር ለሕይወታችሁ የተናገራችሁ እጅግ በጣም አስፈላጊ የሆኑ ድርጅታዊ መልዕክቶች ምን ምን ነበሩ?

1.
2.
3.

እግዚአብሔር እንደ አንድ መሪ እንድትሰሩት የነገራችሁን ነገር ተግባር ላይ እንዳታውሉ በመሰረታዊነት እንቅፋት የሆኑ ድርጅታዊ ነገሮች ምን ምን ናቸው?

1.
2.
3.

ከሰማያዊው መምህራችሁ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በሚኖራችሁ ትብብር ድርጅታችሁ፤ በአርአያነት ወደ መምራት መንገድ እንዲገባ ወይንም በአርአያነት የመምራት መንገድን እንዲያሳድግ ምን ምን ነገሮች አፋጣኝ ትኩረት ያሻቸዋል?

1.
2.
3.

በአርአያነት መምራት በድርጅታችሁ ውስጥ ለመጀመር ወይንም ለማሳደግ ድርጅታችሁ ሊያደርጋቸው የሚችሉ የተለያዩ ነገሮችን ጥቀሱ፡፡

1.
2.
3.


© 2016 MentorLink International

## ለአሰልጣኞች ቡድን ያላችሁ ጥቆማ

በዚህ ስልጠና ውስጥ ሊለወጡ ወይም ሊሻሻሉ የሚገቡ ብላችሁ ለሜንቱርሊንክ የአሰልጣኞች ቡድን ልትጠቁሙ የምትፈልጉትን ነገሮች ከዚህ በታች ዘርዝሩ። ከዛም ለቡድኑ አባላት ይህንን ወረቀት ስጡ።

1.
2.
3.
4.
5.


© 2016 MentorLink International